ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 2፣ መጋቢት 2007

## የህይወት ትርጉም በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

## እኛ እንዲህ እንላለን … 7

አበባው ይርጋ አዳሙ (ዶ/ር)

## “እኔ የተነሳሁት ማሕበረሰቡን ለመጥቀም ነው፡፡”

ንብረት አስራደ (ዶ/ር)

## ጠለፋ … 11

ሂሩት አድማሱ

## የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ … 6

ፈታሒ በቃሉ

## የግጥም ጥግ … ገጽ 13

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖሊ ፔዳ ማስተር ፕላንን ይፋ አደረገ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም ከቀዳሚዎቹ አስር የአፍሪካ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን የያዘውን ራዕይ እና የተማረ የሰው ኃይል የማፍራት ተልእኮ ለማሳካት የሚያስችለው የፖሊ ፔዳ የተቀናጀ የዩኒቨርሲቲ ከተማ ማስተር ፕላን ይፋ አደረገ፡፡ … ገጽ 5ን ይመልከቱ



A ceremony held at BDU’s Administration Head Quarter to introduce the new conceptual master plan

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ተካሄደ ገጽ 5



## አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ተከበረ … ገጽ 4

## ፋኩልቲው ሁለተኛውን አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ … ገጽ 4

## ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት ተደርጓል … ገጽ 4

እውነትን መፈለግና ስሲሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility

# ናይል ጋዜጣ


**በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**
**የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
አብነት ሰለሞን

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
አበባው ይርጋ (ዶ/ር)
ሂሩት አድማሱ
ዋለልኝ አየለ
አረጋዊ ሰለሞን

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው



ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

### ማህበራዊ ችግሮችን ስናነሳ ለዘላቂ መፍትሄውም አብረን መስራት ያስፈልጋል!

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በየዓመቱ እ.ኤ.አ መጋቢት 8 (March 8) ይከበራል፡፡ ዘንድሮም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመቶ አራተኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለሰላሳ ዘጠነኛ ጊዜ ተከብሯል፡፡ ቀኑ ሲከበር ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር የከፈሉት ዋጋ ይታሰባል፡፡ አሁን ላይ ያለው ትውልድ ስለሴቶች ነፃነት፣ መብትና እኩልነት እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡ ብዙ ምሁራን እንደሚናገሩት ሴቶችን መብቃት ማህበረሰብን ማብቃት ነው፡፡ አንድን ሴት ከጥቃት መካከልም እንዲሁ መላውን ቤተሰብ ከአደጋ መታደግ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ርብርብ ይጠይቃል፡፡

ሴት እናት፣ ሚስት፣ እህት፣ ሁሉም ነገር ናት፡፡ ሀገር በሴት ይመሰላል፡፡ ለሴት ልጅ ክብር ስንሠጥ በሴቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከል ስንነሳ የጋራ ደህንነታችን ይረጋገጣል፡፡ ተጠቃሚነታችንም በዚያው መጠን ይጎለብታል፡፡

ሴቶች ላይ የሚደርሱ አስገድዶ መድፈር፣ ፆታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ጥቃቶች ከመድረሳቸው በፊት ለመከላከል ማህበረሰቡ ያላሠለሠ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ እነዚህ ጥቃቶች በተጎጂዎቹ ላይ የሚያስከትሉት አካላዊ፣ ማህበራዊና አእምሯዊ ተፅእኖው ከፍተኛ በመሆኑ ጉዳቱ የሴቶች ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ማህበረሰብ የሚነካ እና ጤና የሚያውክ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ችግሮችን በጋራ በመወያየትና ችግሮችን ከሥራቸው በማድረቅ የእኔነት ስሜት በሁሉም ማህበረሰብ መስረጽ አለበት፡፡ መጋቢት ስምንት የሴቶች ቀን ተብሎ ቢሰየምም ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናቶች (አመቱን ሙሉ) መታወስና ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች የአንድ ሰሞን ወሬዎች በመሆን ያልፋሉ፡፡ እየተረሱም ይቀራሉ፡፡ ጉዳዩ የት እንደደረሰ እንኳን የሚከታተል አካል ጠፍቶ ፍትህ ይጓደላል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ወቅታዊ ብቻ መሆን የለባቸውም፡፡ አሁን አሁን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን የሚሰጣቸው የሴቶች ጥቃቶች ዘግናኝና ለሰሚውም ግራ የሚያጋቡ ጉዳዮች በመሆናቸው ሁላችንም ሲያነጋግረን ሰንብቷል፡፡ አሁንም እያነጋገረን ይገኛል፡፡ ነገር ግን በመገናኛ ብዙሃን የሚዘገቡት እነዚህ ጉዳዮች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ጥቃቶች ሊያሳዩን አይችሉም፡፡ በመገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡት ለፀጥታና ለፍትህ አካላት ሪፖርት የተደረጉትን ብቻ ያጠቃለለ ነው፡፡ ሌላውን ቤት ይቁጠረው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ትኩረት የሚሰጣቸው አካል እስኪጠፋ ድረስ ጊዜ ሲያልፍ እየተረሱና ሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ እስኪመጣ ድረስ ሰሞነኛ ወሬ ብቻ ሆነው ያልፋሉ፡፡ እዚህ ላይ ልናተኩርበት የሚገባን ጉዳይ እነዚህን ጉዳዮች ‹የእኔም› ናቸው በማለት ከስር ከመሰረቱ ለመከላከል ሁሌም አዳዲስ መረጃዎችን መስማት አይጠበቅብንም፡፡ ችግሩን መፍታት የምንችለው ከእኔ ምን ይጠበቃል የሚለውን ጥያቄ መመለስ ስንችል ነው፡፡ ሁሌም የለውጥ አካል መሆን ይገባናል፡፡ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለለውጥ መነሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ሴቶችን ከፆታዊ ጥቃትና ትንኮሳ መከላከል የሁሉም አካል ኃላፊነት መሆን አለበት፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ሁላችንም በየፊናችን የምናያቸውን ጉዳዮች መፍትሔ ለማምጣት በግልፅ እየተነጋገርን፤ ለለውጥ መነሳት እንዳለብን የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡

**እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

## ቁልፍ መልዕክት

### የህይወት ትርጉም በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

እያንዳንዳችን እንድንፈጠር ያደረጉ ተገጣጣሚ ጉዳዮችን በማንሳት የመገጣጠም ዕድላቸውን ስናሰላ በጣም ትንሽ ዕድል እንዳላቸው በስታቲክስ ህግ መረዳት ይቻላል፡፡ አባታችንና እናታችን የመፈጠር፣ የማደግ፣ የመፈቃቀር፣ የመጋባት፣ የመፀነስና ወልዶ የማሳደግ ሂደቶችን በሙሉ ሊያስቀሩ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች እንደነበሩ መረዳት አያስቸግርም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያዊ የተማርነውን ትምህርትና አሁን እየሠራነው ያለውን ስራ የማግኘት ዕድልም በስትስቲክስ ህግ ሲሰላ ዜሮ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ለመሆኑ በዚህ ዕድል የሌለ በመሰለው መንገድ ሄደን አሁን ያለንበትን ሁኔታ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? የሚለውን ለመተንተን አንሞክርም፡፡ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን ግን መገመት ይቻላል፡፡ የዚህ ጽሑፍ አላማ በዚህ እጅግ በጠበበ መስመር የመጣችው ህይወት ትርጉሟ ምን ይሆን የሚለውን ጥያቄ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ እንዲወያይበትና በተለይም ከራዕይ ጥበብ 2017 አኳያ ያለውን ትርጓሜ በማስቀመጥ ውይይት ለመፍጠር ነው፡፡

የህይወትን አላማ ለመረዳት በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ የተለያዩ እይታዎችም ቀርበዋል፡፡ የኔ የመፈጠር ምክንያት ምንድን ነው? ምን እንድሠራ ነው የተፈጠርኩት? በመልሱስ እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል? ብለው በመጠየቅ የተለያዩ ፀሐፊዎች ዕይታቸውን ገልፀዋል፡፡ የሚያዩበት መነፀርም እንደሰለጠኑበት የትምህርት መስክ የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዶቹ በሳይንስ መንገድ ሌሎች ደግሞ ሞራልና ማህበራዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርቡ አሉ፡፡

ለዚህ ጽሑፍ የሚጠቅመው እይታ ህይወትን ከባለቤቱ/ቷ የውስጥ የህይወት ፍላጎትና የህይወት አላማ ጋር በማስተሳሰር የሚገለጽበት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ትርጉም ያለው ህይወት ለግልጽ አላማ የሚሰራና አላማውም በማንም ተጽዕኖ የመጣ ሳይሆን በእውነተኛ የውስጥ ፍላጐት የተመሰረተ ነው፡፡ የሚቀመጠውም አላማ በከፍተኛ ደረጃ የተጠቃለለና የቀን ተቀን ዝርዝር ስራችንን ከዚህ ትልቅ አላማ አኳያ እየተረጐሙ በነዚህ በተፈፀሙ ተግባራት እርካታ ሲገኝ ነው፡፡ ስለአጠቃላይ የህይወት ትርጉም በዚህ ከግለሰቡ/ቧ የህይወት አላማ በግልጽ መኖርና ድርጊትንም ይኸን ከማሳካት አኳያ የመቃኘትና በጠንካራ ዲሲፕሊን የመምራት ጉዳይ ነው ካልን በራዕይ ጥበብ 2017 የስራ ህይወታችን ትርጉም ምን ሊሆን እንደሚገባ ማስቀመጡ ተገቢ ነው፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017 ዩኒቨርሲቲያችንን በሀገራችን አጠቃላይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ላይ የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ተቋም ማድረግ ላይ ያለመ ራዕይ ነው፡፡ የእያንዳንዳችን የስራ ህይወት ትርጉም መቃኘትና መመዘን ያለበት ከዚህ የተቋም አላማና ከራሳችን የህይወት አላማ መጣጣምና መስተጋበር አኳያ ሊሆን ይገባል፡፡ የውስጥ የህይወት ፍላጐቱ ህብረተሰብን ማገልገል የሆነ የዩኒቨርሲቲያችን ባልደረባና የተፈጥሮን ምስጢር ለማወቅ ሌት ተቀን የሚሠራ ተመራማሪ እንደየመረጡት መስክ ትርጉም ያለው የስራ ህይወት ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡ ህብረተሰብን ማገልገል ፍላጐቱ የሆነው ሰው አስተማሪ ከሆነ ተማሪዎችን በሚገባ ይዞ የሚያረካ ትምህርት በመስጠት፣ የቢሮ ውስጥ ኃላፊ ከሆነ ደንበኞችን በሚገባ በማገልገል የውስጥ ፍላጐቱንና የተቋሙንም ፍላጐት በማሳካት ትርጉም ያለው ህይወት መመስረት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተፈጥሮን መመርመር ፍላጐቷ የሆነች ተመራማሪ ስራዋን በሰከነና ጠንካራ ትኩረት ባለው መልኩ በመስራት በአንድ በኩል የውስጥ እውነተኛ ፍላጐቷን ማርካት ትችላለች፡፡ የራዕይ ጥበብ 2017ን አላማም የሚደግፍ ተግባር ነው፡፡ ለመሆኑ ይህ ገለፃ ምን ያስተምረናል ብሎ መጠየቅ ሊኖር ይችላል፡፡

ህይወታች እጅግ በጣም አጭር ናት፡፡ ከአንዳንድ የተፈጥሮ ዕድሜዎች ጋር ስናነፃጽረው አይንን ከፍቶ ወዲያውኑ ከመዝጋትም ያጥራል፡፡ ያነሳነው ጥያቄ ይች ብልጭ ብላ ድርግም የምትለው ህይወታችን ትርጉሟ ምንድን ነው? ብልጭ ባለችበትስ ቅጽፈት ምን መስራት ይገባናል የሚሉ ሀሳቦችን በማንሳት ለህይወታችን ትርጉም የምንሰጥበትን አግባብ እርስ በርሳችን እንድንመማርበት ያግዘናል፡፡ በተጨማሪም ራዕይ ጥበብ 2017 የስራ ህይወታችንን ከፍተኛ ትርጉም እንዲኖረው የሚያግዝ ራዕይ ነው፡፡ በመሆኑም ራዕዩን በሚገባ ተገንዝቦና ከራሳችን የህይወት አላማ ጋር በማጣጣም የማያልፍ አሻራ የምንጥልበትን ዕድል ለማስፋፋት ነው፡፡ ሰዎች ኃላፊዎች ስለሆን የማያልፍ ስራ ለመስራት ያብቃን፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!!!**

# አበይት ዜናዎች...

## አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ተከበረ

በአበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት አለም አቀፉን የሴቶች ቀን አከበረ፡፡ በበአሉ አከባበር ስነ ስርአት ላይ ውይይት፣ የተጋባዥ እንግዶች የሕይወት ተሞክሮ፣ የሴት ተማሪዎች አምባሳደር ምርጫ እንዲሁም የተለያዩ ስፖርታዊ ዝግጅቶች ቀርበዋል፡፡

የባሕር ዳር አካዳሚ መስራችና የኢትዮጵያ እስኩል ሚል እንሼቲቭ ዳይሬክተር ወ/ሮ ፍሬአለም ሽባባው የህይወት ተሞክሯቸውን ለተሳታፊዎች ያካፈሉ ሲሆን ሴቶች ወደ ከፍተኛ ደረጃ እየወጡ ተሳትፎአቸው እያደገና ተፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡ በተለያዩ አመራርና ትላልቅ ቢዝነሶች እየሰሩ ያሉትን ሴቶች ራሳቸውን ጨምረው በማሳያነት አቅርበዋል፡፡ ሴቶች በተናጠልም ሆነ ተደራጅተው የመንቀሳቀስን አስፈላጊነትን አጉልተው ያነሱት ወ/ሮ ፍሬአለም በመንግስት በኩል ለሴቶች የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በማሳያነት ጠቅሰዋል፡፡

ሴቶች ስኬታማ ለመሆን ምን መስራት እንዳለባቸው አቅጣጫ በማሳየት ሕብረተሰቡን እንዴት እናገለግላለን፣ አካባቢንና አገርን እንዴት እንቀይራለን፣ ማሕበራዊ ስርአቶችን እንዴት ባለ መልኩ ይደራጅ የሚሉትን ጉዳዮችን እያነሱ ለመውያየት መሰል መድረኮች ሊዘጋጁ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ራስን ፈልጎ ማግኘት የሴቶች ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል ያሉት ወ/ሮ ፍሬአለም ለደሞዝ ሳይሆን ለእርካታ መስራት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ ወጣት ሴቶች የሚያረካቸውን የስራ መስክ ለማወቅ ጊዜ ወስደው ማሰብ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡ ለገንዘብና ለተለያዩ ነገሮች ተገዥ ሳይሆኑ ሃላፊነትን ለመወጣት መጣር፣ ስራዬ ማንን ጠቀመ ማንን ቀየረ ማለት ይበልጥ ተገቢነት እንደሚኖረው ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር ማተቤ ተፈራ በውይይቱ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉ ሲሆን ጥሪ የተደረላቸው እንግዶችና ተሳታፊዎች የፕሮግራሙ መልዕክት አስደሳችና አስተማሪ እንደነበር ገልጸው ወደፊትም እንዲህ አይነቱ መድረክ መፍጠር ተገቢ እንደሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡ ፡

## የሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ሁለተኛውን አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ

በአበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ በቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍ፣ ባሕልና ተግባቦት ዙሪያ ላይ ያተኮረ ሁለተኛው አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

በአውደ ጥናቱ የመክፈቻ ፕሮግራም በክብር እንግድነት የተገኙት የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዩች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ምላሽ ለሚያሻቸው ጉዳዮች ምላሽ የሚገኝበት እንዲህ አይነቱ የውይይትና የምክክር መድረክ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል፡፡ መድረኩ በመማር ማስተማሩም ሆነ በምርምር ጅምር ጥረታችንን ወጤታማነት ላይ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ጉልህ በመሆኑ ቀጣይ ዝግጅቱ በተጠናናነ በተደራጀ መልኩ መመራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

የሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ስዩም ተሾመ በበኩላቸው ከመጀመሪያው አውደ ጥናት ልምድ በመቅሰም የተሻለ ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰው ምሁራን ጥናታዊ ፅሁፎችን እንዲያቀርቡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥሪ መደረጉን አመልክተዋል፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ በመማር ማስተማርና በምርምር ዘርፍ የተለያዩ ስራዎች እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡

በዩኒቨርስቲው ፔዳ ግቢ አዳራሽ መጋቢት 4 እና 5 በተካሄደው አውደ ጥናት የተለያዩ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሄዶባቸዋል፡፡ ከቀረቡት ሃያ አምስት ጥናታዊ ፅሁፎች 56 በመቶ በዩኒቨርሲቲው መምህራን ቀሪዎቹ ደግሞ በሌሎች ተጋባዥ ምሁራን ቀርበዋል፡፡ በጥናታዊ ፅሁፎች ዙሪያ በርካታ ጥያቄዎች ከተሳታፊዎች ተነስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ፋኩልቲው 4 የቅድመ ምረቃ፣ 7 የድህረ ምረቃ 2 የሶስተኛ ዲግሪ መርሃ ግብሮች ሲኖሩት በውስጡም 93 መምህራን፣ 6 የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም 45 የአስተዳደር ሰራተኞች 3716 ተማሪ በማስተናገድ ላይ ይገኛል፡፡

## ለአይነ ስውራን ተማሪዎች መሰረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና ተሰጠ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለሚማሩ ዓይነ ስውራን ለአስር ተከታታይ ቀናት የቆየ የመሰረታዊ ኮምፒውተር ስልጠና ተሰጠ፡፡

ስልጠናው የተዘጋጀው የመማር ማስተማሩን ሂደት ለአይነ ስውራኑ ምቹ ለማድረግ፣ የትምህርት መረጃዎችን እንደማንኛውም ተማሪ አንብበው እንዲረዱ፣ ከመምህራኑ የሚሰጡ የቡድንና የተናጥል ስራዎችን ለመስራት የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባጠቃላይም ጥገኝነት እንዲላቀቁና ዘላቂ ህይወታቸውን በአግባቡ እንዲመሩ ለማስቻል የተዘጋጀ ሲሆን ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው አቅም ግንባታ ማዕከል ተሰጥቷል፡

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ማህበሩ በዩኒቨርሲቲው አመታዊ ጉባዔውን አካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የኢትዮጵያ ስነ ሕይወት ባለሙያዎች ማሕበር 25ኛ አመታዊ ኮንፈረንስ “ECO-Tourism in Ethiopia a better alternative to BiO-divesity Concervation” በሚል መሪቃል ከመጋቢት 11-12/ 2007 በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተከበረ፡፡

የማሕበሩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ውቤ የኢትዮጵያ ስነ ሕይወት ባለሙያዎች ማሕበር የዛሬ 26 ዓመት በ30 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስነ ሕይወት ትምህርት ክፍል መምህራን መቋቋሙን አስታውሰው ማሕበሩ በዋናነት የባለሙያዎችን ጥናታዊ ፅሁፎች ለማየት፣ ተመራማሪዎች ችግር ፈች ርዕሶችን

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት ተደርጓል

- ስልጠናው በሕይወት ክህሎት፣ የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት እና ኤችአይቪ ኤድስ ዙሪያ ያተኮረ ነው

በአምሳሉ ጥላሁን እና በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዐተ-ፆታ ጽ/ቤት በዩኒቨርሲቲው ላሉ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሕይወት ክህሎት ስልጠና ሰጠ፡፡ በተመሳሳይ የዩኒቨርሲቲ ኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክትሬት ከዲኬት ኢትዮጵያ ጋራ በመተባበር ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተቀናጀ የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት እና ኤችአይቪ ኤድስ ዙሪያ የአንድ ቀን ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በስልጠናው ላይ የተገኙት የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ምህረቴ ዋለ ዩኒቨርሲቲው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የተለየ ትኩረት በመስጠት የቁሳቁስ የገንዘብ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ገልፀው ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎቹን ችግር ለመፍታት ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ በመቅሰም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ስልጠናው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በራስ የመተማመን ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ፣ ከሰዎች ጋር ያላቸው ተግባቦት እንዲጨምር፣ የሕይወት ግባቸው እንዲሰምር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ታስቦ እንደተዘጋጀ አስታውቀዋል፡፡

የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲውም ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ባሉ አንዳንድ ወገኖች ችግሮች ሊገጥሟቸው እንደሚችሉ የጠቀሱት አቶ መሰረት አያሌው በበኩላቸው ስልጠናው አካል ጉዳተኞቹ በስነልቦና ዝግጁ ሆነው መፍትሄ እንዲሹ የሚያደርጋቸው ነው ብለዋል፡ ፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልቦና መምህር የሆኑት አቶ መሰረት አያሌው አክለውም ስልጠናውን በመማር ማስተማሩ ሂደት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ውጤታማነት ይበልጥ የተቃና እንደሚያደርገው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ዜናዎቻችንን በድረ-ገጻችን **http://www.bduinfo63@bdu.edu.et** ወይም http://www.bdu.edu.et እና በፌስቡክ ገጻችን www.facebook.com/bdu-ethiopia መከታተል ይችላሉ፡፡

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲው የፖሊ ፔዳ ማስተር ፕላንን ይፋ አደረገ

በታድዬ አስማረ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም ከቀዳሚዎቹ አስር የአፍሪካ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን የያዘውን ራዕይና ተልእኮ ለማሳካት የሚያስችለው የፖሊ ፔዳ የተቀናጀ የዩኒቨርሲቲ ከተማ ማስተር ፕላን ይፋ አደረገ፡፡

ወ/ሮ ገነት ገ/እግዚአብሄር የክልሉ ከተማ ልማት ዳይሬክተር እና የዩኒቨርሲቲው የቦርድ አባል የክልሉን መንግስት በመወከል በስነ ስርዓቱ ላይ እንደተናገሩት የሀገራችን ከተሞች ዘመናዊነትን የተላበሱ አይደሉም፡፡ ለከተሞቻችንን ዘመናዊነት ለማላበስ በማስተርፕላን መመራት ይገባል፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በፋና ወጊ እንቅስቃሴው ዩኒቨርሲቲውን የዩኒቨርሲቲ ከተማ ለማድረግ እና የባሕር ዳር ከተማን ለማፋጠን የሚያስችል ማስተር ፕላን አሰርቷል፡፡ በክንውን ሂደቱ የክልሉ መንግስት ድጋፍ አልተለየውም ወደፊትም አይለየውም ብለዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ይፋ ያደረገውን ይህንኑ የተቀናጀ የዩኒቨርሲቲ ከተማ ማስተር ፕላን እውን በማድረግ ሂደት ማሕበሩ ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከቱን አስታውቀዋል፡፡ ማሕበሩ በፕላን ዝግጅቱ ሂደት የሚሳተፉ ባለሙያዎችን ለመመልመል የሚረዳ ሙያዊ መስፈርት አዘጋጅቶ ባለሙያዎችን በማወዳደርና በማማከር ስራዩኒቨርሲቲውን የወደፊት ራዕይ እንደሚያሳካ ታምኖበት ከኢትዮጵያ አርክቴክቸሮች ማሕበር ጋር በትብብር የተዘጋጀው ይህ የተቀናጀ የዩኒቨርሲቲው ከተማ ማስተር ፕላን ከፖሊ ቴክኒክ ግቢ እስከ ፔዳ (ዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ ያለውን ሰፊ መልክአ ምድር ያካልላል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በምርምሩና በሰው ኃይል ልማቱ ዘርፍ ልቆ ለመወጣት የሰነቀውን ራዕይ እውን ለማድረግ በነደፈው ዕቅድ መሰረት ለማስተር ፕላኑ የሚያስፈልገውን መሬት ከክልሉ መንግስት ጠይቆ ተገቢውን ምላሽ አግኝቷል፡፡

በዚህ ረገድ የቀድሞው የክልሉ ርዕሰ አስተዳደር የአቶ አያሌው ጐበዜና የካቢኔያቸው ድርሻ ጉልህ ስፍራ መያዙን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በስነስርዓቱ ላይ ካደረጉት ንግግር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የማስተር ፕላን መሰራት የዩኒቨርሲቲውን መሰረታዊ አላማዎች ከመሳካት ባለፈ ባሕር ዳር ከተማን ዘመናዊነት እንደሚያሳውቅ መሳተፉን አመልክተዋል፡፡

ከዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ ጋር በመተባበርም ለባለሙያዎቹ ከዩኒቨርሲቲው ተልዕኮና ራዕይ ጋር የሚጣጣሙ መረጃዎችን በማሰባሰብ ባለሙያዎች በመረጃ የተደገፉ ስራዎች እንዲሰሩ ማድረጉንም አስገንዝበዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የቢዝነስና ልማት ም/ፕሬዚዳንት አቶ መንግስቱ ገብሩ ማስተር ፕላኑን ለማሰራት ዩኒቨርሲቲው የጨረታ ሰነዱን በአለማቀፍ ደረጃ ማውጣቱን ጠቅሰው በሂደቱ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በማበረታታት ከውጭ ባለሙያዎች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ተናግረዋል፡፡ በዚህም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ተቀናጅተው ስራውን እንዳከናወኑት አስታውቀዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የከተማ ማስተር ፕላን ለመስራት አስራ አምስት ድርጅቶች በጨረታው ሂደት ተከፍለው ዘጠኙ በመወዳደሪያ መስፈርቶች ተለይተዋል፡፡ ከነዚህ መካከልም አምስቱ በባለሙያተኞች ተመርጠዋል፡፡

## ለሬጅስትራር ሠራተኞች ስልጠና ተሰጠ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር አሉሙናይ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት በአዲሱ የሰው ሀይል ድልድል መሰረት ወደ ክፍሉ ለተመደቡና አዲስ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የአቅም ማጐልበቻ ስልጠና ሰጠ፡፡

ደንበኛ ተኮር የሆነ አሰራርን በማስፈን በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ብሎም የደንበኞችን ፍላጐት የሚያረካ አሰራር ለማስፈን ታስቦ የተዘጋጀው ይህ ስልጠና በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በነበረው የአራት ቀናት ቆይታ ስለ አካዳሚክ ሬጉሌሽን

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም ተካሄደ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

በአማራ ክልል የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዘጠንኛውን ፎረም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት የመሰብሰቢያ አዳራሽ አካሄደዋል፡፡

የፎረሙ መደበኛ መርሃግብር የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ተጀምሯል፡፡ ሰባቱም የክልሉ ዩኒቨርሲቲዎች የጠበቀ የርዕስ በርዕስ ትስስር እንዳላቸውና አኩሪ ተግባራትን ለማከናወን እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ መሆናቸው የጠቀሱት ዶ/ር ባይሌ ፎረሙ በጋራ እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡ በተቋማቱ በተፈጥሮ፣ በባሕል፣ በአገራዊና በአለም አቀፋዊ ሀይል ላይ የሚሰሩት ምርምሮች የሰለጠነውን የሰው ሀይል ወደ ተማሪ በማሳሳብ እንቅፋት የሚሆኑትን ሀይሎች ወደ ጥቅም የመቀየሩ ተፅኖ በአፍሪካ ብሎም በአለም ላይ ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አያይዘውም ፎረሙ ለዘጠንኛ ጊዜ እየተካሄደ እንደመሆኑ መጠን ታሪካዊ ጉዞው ምን እንደሚመስልና ተጨማሪ ውሳኔ በሚያሻቸውና በሚሻሻሉ ሀሳቦች ላይ በጋራ ውይይት ጥሩ ውጤት ላይ መድረስ እንደሚቻል በተጨማሪም ችግር ፈቺ የሆነ ምርምር ለማካሄድ ዋናው ትጥቅ «እውቀት» ነውና ከዩኒቨርሲቲዎች የሚወጡ ምሁራን የተማረ ብቻ ሣይሆኑ የተማሩና የሰለጠኑ መሆን እንደሚገባቸው በመገንዘብ ሁሉም የሰነቀውን ራዕይ ለማሳካት በፎረሙ ቆይታ ገደብ የለሽ ውይይት እንዲካሄድ አሳስበው ዩኒቨርሲቲውን ከማስተዋወቅ አንፃር የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምር ባህሉ ለማድረግ የምርምር ተቋማት መቋቋማቸው፣ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች በፊጣን ለውጥ እየተስፋፉ መሆናቸውን እንዲሁም ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እየተከናወነ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በፎረሙ የተሳተፉት ከሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ አመራሮች፣ የቦርድ አባሎችና ተማሪዎችን ከመርሃ ግብሮች አንዱ የሆነውን የመስክ ጉብኝት አካሄደዋል፡፡ በቅድሚያ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ሳይንስ ኮሌጅ ጢስ አባይ ግቢ የተጎበኘ ሲሆን የህንፃው አማካሪ አልትሜት ፕላን አርክቴክቶች መሀንዲስ አቶ አክሊሉ ተክለብርሃን ግንባታው ያለበትን ደረጃ አስረድተዋል፡፡ የሆስፒታሉ ግንባታ 70% መከናወኑንና ቀሪውን ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ዶ/ር ባይሌ ሆስፒታሉ ከመማር ማስተማሩ ጐን ለጐን ለአካባቢው ማሕበረሰብ የተሻለ የሕክምና

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## መፅሐፍ ተመረቀ

በታድዬ አስማረ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ የታሪክ መምህር የሆኑት ዶ/ር ፋንታሁን አየለ "የደርግ መንግስት መከላከያ ሰራዊት አነሳስና ውድቀት" በሚል ርዕስ ለሶስተኛ ዲግሪያቸው የጻፉትን የምርምር ስራ በመፅሐፍ መልክ አዘጋጅተው አስመረቁ፡፡ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተከናወነው የመፅሐፍ ምረቃ ስነስርዓት ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው መፃሕፉን ለማስመረቅ በሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ የታየውን ተነሳሽነት አድንቀው ወደፊት እንደአስፈላጊነቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለማስመረቅ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የዶ/ር ፋንታሁን መልካም ጅምር ለሁሉም የዩኒቨርሲቲው መምህራን ተነሳሽነትን ይፈጥራል፡፡ የመጽሐፉ መታተም የአገር ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው አብራርተዋል፡፡ በዚህ መሰሉ ተግባር ለሚሰማሩ መሰል ምሁራን ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑንም ዶ/ር ተስፋዬ ገልፀዋል፡፡

የመፃሀፍ ጠቅላላ ይዘት በምሁራን ተገምግሞ የቀረበ ሲሆን በተለይ የታሪክ ምሁራኑ አቶ ታረቀኝ አለሙ እና ዶ/ር ገድፉ አበዋ በጥልቀት በማንበብ ለተሳታፊው አጠቃላይ ግምገማቸውን አቅርበዋል፡፡ እንደምሁራኑ ገለፃ በሰባት ምዕራፍ የተከፋፈለ የዶ/ር ፋንታሁን መፅሐፍ በርካታ ማስረጃዎች እንደተካተቱበት ተመልክቷል፡፡

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከጥር ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ተስፋሁን በፖሊስ ጣቢያ በቁጥጥር ሥር ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ እዚያው ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚያየው ትዕይንት እየተገረመ ነው። ፖሊሱ ደግሞ የሥርቆት ተግባሩን እንዴት ሊፈፅም እንደቻለ እንዲናገር ሌላ የቤት ሥራ ሰጥቶታል።

ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ እንደገና ተጠራሁ። ስወጣ ሣጅን እና ሌሎች ጓደኞቼ ብርድ ልብስ፣ አንሶላና ለመኝታ የሚያገለግል ምንጣፍ እንደዚሁም የታሸገ ውኃ እና ፍራፍሬ ይዘው ቆመዋል። ሲያዩኝ በሩቁ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረቡልኝ። በመቀጠልም ቀልደኛው ጓደኞችን ‹‹እንዴት ነው? ሰው ተክቶ መውጣት አይፈቀድም? የሚቻል ከሆነ ለነገ እኔ ልታሠርልህ ሙሉ ፈቃደኛ ስለሆንሁ አጣርተህ ንገረኝ።›› በማለት ሲቀልድ፣ እዚያ የቆመው ፖሊስም አብሮ ሣቀና፣ ‹‹ሰማህ ወንድም በጉዳዩ ካለህበት፣ አብሮ መታሠር እንጅ ተክቶ መታሠር አይቻልም እና እንደዚህ ጥብቅ ቁርኝት ካላችሁ ጉዳዩን ለማጣራት ስለሚጠቅም ለፖሊስ ጣቢያው አዛዥ እንነግረውና መልሱን እናስታውቅሃለን፤›› በማለት ሲናገር መለሰና ‹‹እንደዚህ ከሆነ ሃሳቤን አንስቻለሁ።›› በማለት እንደገና አሣቀን።

በዚህ ሁኔታ እያወራን እያለን ሌሎችን እሥረኞች ለመጠየቅ ብዙ ሰዎች ስለመጡ ፖሊሱ፣ እነሱን ለማስተናገድ ሲል ‹‹ይበቃል። ተመለሱ›› አለና እያንዳንዷን የሚሰጡኝን ነገር እየፈተሸ ሰጠኝና ጠቅልዬ በመያዝ ቅር እያለኝ ወደ እስር ቤቱ ውስጥ ገባሁ። ሊጠይቁኛ የመጡት ጓደኞቼም የትካዜ ስሜት እየታየባቸው ተመልሰው ሄዱ። ወዲያው የግቢውና የጓደኞቼ ሁኔታ ፍንትው ብሎ አንድ ባንድ ሲታየኝ ጭንቀት ለቀቀብኝና ‹‹የግል ነፃነት ማጣት በራሱ ምን ያህል አስቸጋሪና አስፈሪ እንደሆነ›› በማሰብ ብቻየን መቆዘም ጀመርሁ።

እየመሸ ሲመጣ ወደ መፀዳጃ ቤት በየተራ እንድንሄድ ተነገረን። እኔም ተራዬ ደርሶ ከስምንት ያላነሱ ሰዎች ጋር ሄድሁና ከመፀዳጃ ቤቱ ስደርስ የማየውን ማመን አቃተኝ፣ በአጠቃላይ ሲታይ በሽንት ቤቱ ላይ ጭቃ ተቦክቶ ለምርግ የተቀመጠ የሚመስል ዐይነ-ምድር ይታያል። በዚያ ላይ የሽንቱ ሽታ ተጨምሮበት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ግራ ያጋባል። ይህንን ስመለከት የነበረኝ የመፀዳዳት ስሜት ጠፋ። ወዲያው ጉንፋኔን ሸምቼ ስለተመለስሁ ደጋግሞ አስነጠሰኝ። እንደተቀመጥሁ አብሮኝ ያለውን እሥረኛ ለምን እንደዚህ እንደሆነ ስጠይቀው፤ ሰው ዳግም ወንጀል ሠርቶ እንዳይታሠር ለማድረግ እንደሆነ አለና… ቀና ብሎ እየተመለከተኝ ለነገሩማ እንዲያ፣ ቢሆን ኖሮ ብዙ ደጋጋሚ ወንጀለኞች ባልኖሩ ነበር፤ ለምሳሌ እነዚያ ከማዕዘን አካባቢ የተቀመጡት አራቱ ወጣቶች የዚህ እሥር ቤት የዘወትር ደንበኞች እንደሆኑ ከሰሞኑ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። ብቻ ያም ሆነ ይህ ለሽንት ቤቱ መበላሸት ዋናው ምክንያት ከሰው ብዛትና ከግዴለሽነት አጠቃቀም ችግር የተነሣ ነው። ስለዚህ እኛ አበሻዎች በጋራ በምንጠቀምባቸው ነገሮች ላይ ግዴለሾች ስለሆንን ይሆናል። በማለት አብራራልኝ።

እየጨለመ ሲመጣ ከጣራው ላይ በጣም የቆሸሸች አምፖል በሩቁ የብርሃን ወጋገኗን መፈንጠቅ ጀመረች። ማን እንዳበራት ባላውቅም፣ የብርሃን መጠኗ ሲታይ፤ ሰው ከሰው እንዳይጋጭ የምታግዝ እንጅ ምን አልባት ሳንቲም ቢወድቅ ፈልጎ ለማግኘት የሚሆን የብርሃን አቅም እንኳን የላትም። ይህን ስገነዘብ በጣም ገረመኝና ለዚች አምፖል ነው ለመብራት ብለው በጥፊና በእርግጫ አስገድደው ብሬን የወሰዱት በማለት ብቻዬን ማሰላሰል ያዝሁ።

በግምት አንድ ሰዓት አካባቢ ሲሆን እዚያ ያለው ሁሉ አልፎ፣ አልፎ ቡድን በመመሥረት ክብ ሠርቶ በመሰባሰብ ራት እየበላ ነው። አጠገቤ ያለው እሥረኛ አብረውት ሲበሉ የሰነበቱት

> አውቶቡስ ተራ ላይ ስትሸኘኝ የነበረው ሁኔታ - በመጨረሻ ስትሰናበተኝ የተናገረችኝ ቃል፣ በጆሮዬ ውስጥ እንዲህ በሚል ይጮህብኛል....‹‹ተስፋሁን አይዞህ! እኔ እናትህ በሕይወት እስካለሁ ለአንተ አላንስም ብቻ በርትተህ ተማር! ...

በአጋጣሚ ተሳክቶላቸው ዛሬ ስለተፈቱ ብቻውን፣ ላለመብላት፣ ከየትኛው ቡድን ጋር ልቀላቀል እያለ ሲያስብ እኔን ስላገኘ ደስ ብሎታል። ‹‹ እናም አንተን ባላገኝ ከማን ጋር እመገብ ነበር?›› አለና የመጣለትን፣ በሣህን የተቋጠረ ምግብ አብረን በላን። ቀጥለንም እነሣጅን ካመጡልኝ ሙዝና ብርቱካን አንዳንድ ያዝንና ቀሪውን በአጠገባችን ላሉት ሠጠናቸው።

እዚያ ያለው ሁሉ እርስ በእርስ ስለሚያወራ ጫጫታው ለጉድ ነው። የምግቡ ሽታም እንደዚሁ። ራት ከተበላ በኋላ ሁሉም በያለበት ሲሣሣቅና ሲጫወት ቆይቶ ቀስ በቀስ በእንቅልፍ እየተሸነፈ ሲመጣ የግድ ያለውድ ጎኑን ለመሬት አደራ መስጠት ያዘ።

ሰው ሁሉ የተኛ ይምሰል እንጅ ይገላበጣል ያካል። መቼም እዚያ ቤት ያለው ቁንጫና ትኋን ስፍር ቁጥር የለውም። እንኳን የተኛውን ተቀምጦ የሚያወራውንም መላ አካሉን ያሳክከከዋል። እኔም ቆዳይን ልጨ ልጥለው ምንም አልቀረኝ። እንዲያም ሆኖ ሰው እንቅልፍ ይወስደዋል። እኔ ግን እንኳን ተባይ ተጨምሮብኝ ተባይ ባይኖርም ለመተኛት አዕምሮዬ ዝግጁ አይደለም።

በዚህ ላይ ሽንቱ የመጣበት ሁሉ ብድግ ይልና ግድግዳውን ተጠግቶ ያለማንም ከልካይ ይሸናል። ምን አልባት አጠገቡ ‹‹የተኛው ኧረ እባክህ በላዬ ላይ እንዳትሸና ካለው›› መብቱ እንደሆነ በመቁጠር ‹‹ታዲያ የታባትህ ላይ ልሸናልህ ትፈልጋለህ›› ይለዋል። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ የክፍሉ ሽታ ምን እንደሚሆን መገመት ነው። ለካንስ ሰው ከእንስሣት የተሻለ ማሰብ የሚችለው የግል ነፃነቱ ተከብሮ እንደልቡ መሆን ሲችል ነው።

አዕምሮዬ በሆነ ባልሆነው እየተጨነቀ ነው። አሁን ያለሁበትን ሁኔታ ስገነዘብ በጣም ይቆጨኛል። ወደ ኋላ ተመልሼ ወደ አገር ቤት ሄድሁ። የእናቴ ልፋትና ለእኔ የነበራት እናታዊ እንክብካቤና ፍቅር ወለል ብሎ ታየኝ። አውቶቡስ ተራ ላይ ስትሸኘኝ የነበረው ሁኔታ፣ በመጨረሻ ስትሰናበተኝ የተናገረችው ቃል፣ በጆሮዬ ውስጥ እንዲህ በሚል ይጮህብኛል....‹‹ተስፋሁን አይዞህ! እኔ እናትህ በሕይወት እስካለሁ ለአንተ አላንስም ብቻ በርትተህ ተማር! የእኔን ያለመማር ቁጭት የምትወጣልኝ አንተ ነህ።›› ያለቸው አሁንም፣ አሁንም እየደጋገመ ይሰማኛል። ከዚያም በአውቶቡሱ ተሳፍሬ ወደ ባሕር ዳር መምጣቴ፣ ሁኔታዎች ተመቻችተው፣ ትምህርቴን ስከታተል በመቆየት በአንደኛው ሴሚስተር ካስመዘገብሁት ከፍተኛ ውጤት፣ ቀጥሎ የመታወቂያዬ መጥፋትና መገኘት፣ የሄርሜላ ትዝታ፣ የሻሼ የዋህነት፣ የምኝታ ቤት ጓደኞቼ ከጥናት መልስ የጋራ ቀልድና ጨዋታ፣ የሣጅን ምክርና ለእኔ ያለው የተለዬ እንክብካቤ እንደዚሁም ሔርሜላን ለማግኘት በነበረኝ ጉጉት ከወዲያ ወዲህ ስባዝን በሌባ መዘረፌ፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ፣ በዚያ ሰበብ በሌብነት ተጠርጥሬ መታሠሬ፣ ተራ በተራ ይመጡብኛል። ዝም ብዬ ሁኔታውን ሳስበው ከዚህ እሥር ቤት ወጥመድ እንዴት እንደምወጣ ሣስበው እየጨነቀኝ መጣ። ምክንያቱም ይህንን ሁኔታ እናቴ ብትሰማ የምታብድ ይመስለኛል።

በዚህ ሁኔታ ሦስት ቀናትን አሳለፍሁ። አሁንም እፈታለሁ የሚለው ተስፋ እንዳለ ነው። በየቀኑ ብዙ እሥረኛ ይፈታል። እንደገና በላይ በላዩ ሌሎች እሥረኞች ይመጣሉ። ብዙ እሥረኞች ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ ወይ በነፃ ያሊያም በዋስ ይፈታሉ። ጉዳያቸው ከበድ ያሉት ደግሞ ፍርድ ቤት ከሄዱ በኋላ፣ መኖ ባለበት ወደ ማረሚያ ቤት ይላኩና የቦታ ለውጥ በማድረግ እዚያ ይታሠራሉ።

በጠዋቱ ዘመድ እንደሚፈልገኝ ፖሊሱ ጠርቶኝ ስወጣ ሻሼ ናት። ሰላምታ ተለዋወጥንና ማን እንደነገራት ስጠይቃት ‹‹ባለፈው ቀጠሯችን መሠረት ማክሰኞ ዕለት ስላልተመቸኝ አንተን በማግኜት ሞባይሏን ለመስጠት፣ ለጓደኛህ የደወልሁት ትናንትና ነበር። እናም በአጋጣሚ ፖሊስ ጣቢያ በቁጥጥር ሥር መዋልህን ነገረኝ›› አለችኝ። እኔም እይውልሽ ባላወቅሁት ነገር ሳላስበው እሥረኛ ሆኛለሁ። ችግሩ የተፈጠረው ያኔ ወደ ሹም አቦ ለመሄድ ታክሲ ውስጥ ስንገባ ሌቦች ዋሌቴን ወስደውብኛል። በማለት ከዚያ ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ክስተት በዝርዝር ነገርኋት። እሷም በጣም አዘነች። ፖሊሱም ዐይኑን ከሻሼ ላይ ተክሎ እየተመለከተ ከሰነበተው በተለዬ ነፃነት ሰጠኝ። ምን ያድርግ ሻሼ በዚያ ቁንጅናዋ ላይ ፀጉሯን ከትክሻዋ በታች ለቃ ስተትታይ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አለባበሷን አሳምራ ተውባ ስለመጣች እንኳን እሱ ወጣቱ በዕድሜ የገፉ አዛውንቶችም ቢያይዋትና ሥራቸውን ቢረሱት አያስገርምም።

ሻሼ ስታወራኝ ቆይታ፣ በሣህን የቋጠረችውን ምግብና ፍራፍሬ አስረክበችኝና ‹‹ለመሆኑ ፍርድ ቤት ቀርበህ ነበር?›› ስትለኝ ፖሊሱ ቀደመና ‹‹ሌሎች መጣራት ያለባቸው ነገሮች ስላሉ አልቀረበም።›› አላት። እሷም እስቲ ስለሁኔታው ፖሊስ አዛዡን እጠይቀዋለሁ አለችና ሌላ ተስፋ ሰጥታኝ፣ በል እንግዲህ እግዚአብሔር ያስፈታህ ብላኝ ሄደች።

ወደ ውስጥ እንደገባሁ ባለፈው ሣጅን ችግር የለም በሁለት ቀን ውስጥ ትፈታለህ አለ። እንኳን ልፈታ ዘወር ብሎም ያየኝ የለም። ዛሬ ደግሞ ሻሼ ፖሊስ አዛዡን እጠይቃለሁ አለች። ነገር ግን ውጤት የሚኖረው ስላልመሰለኝ ለብቻዬ በኃሳብ ዓለም እዋኛለሁ።

ከሰዓት በኋላ እነሣጅን የተለያዩ ሃንድ አውትና የእኔን ደብተሮች ይዘው በመምጣት ፈተና እየደረሰ ስለሆነ፣ በተቻለህ መጠን ለማንበብ ሞክር፤ ሌላውን ስትመጣ በጋራ ዲስከስ እናደርጋለን በማለት ከአንድ ሣህን ምግብ ጋር አስረከቡኝ። በመቀጠልም ባለፈው የተሰጠንን አሣይሜንት ለመምህሩ አጠናክረው ማስገባታቸውንና በብዛት የተጠቀሙበት የእኔን ጽሁፍ እንደነበር ሞራል በመስጠት አድናቆታቸውን ገለፁልኝ። ከዚያም ትንሽ ሲያወሩኝ ቆይተው ተሰናብተውኝ ሄዱ።

የተቀበልሁትን ማተሪያል አጠገቤ ያለው እሥረኛ አየና፣ የምን ተማሪ እንደሆንሁ ሲጠይቀኝና ስነግረው በደንብ ማንበብ እንዳለብኝ አጥብቆ መከረኝ። እኔም እዚህ ቦታ ሆኘ እንዴት አድርጌ ማንበብ እችላለሁ ስለው፣ ለሱ ችግር የለም አንተ አዕምሮህን ለማንበብ ካዘጋጀኸው አስፈቅደህ ከዚህ ክፍል ውጭ ከጠባቂ ፖሊሶች ጋር ቁጭ ብለህ ታነባለህ በማለት ፍንጭ ሰጠኝ። ወዲያው በሁኔታው በመስማማት እሱ በነገረኝ መሠረት ሁኔታውን ለጥበቃ ፖሊሱ ስነግረው ፈቀደልኝና ከዚያች ፖሊሶች ከሚጠብቁባት ጠባብ ክፍል ውጭ በበረንዳው ቁጭ ብዬ ማንበብ ጀመርሁ። መጀመሪያ በመፈታቴና ባለመፈታቴ መካከል የተዘበራረቀ ኃሳብ ስለመጣብኝ የማልፈታ ከሆነ ለምን አነባለሁ፣ አልሁና መልሼ ምን አልባት የመፈታት እድል ካጋጠመኝ መዘጋጀቱ ጉዳት የለውም፤ በሚል እሳቤ ማንበቤን ቀጠልሁ። ማንበብ በመጀመሬ በተለያዩ ኃሳቦች ተወጥሮ የነበረው አዕምሮዬ በመጠኑ እየተረጋጋልኝ ስለመጣ የማነበው ነገር ሁሉ ግልፅ እየሆነልኝ ይመጣ ጀመር። በመሆኑም እሥር ቤት ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ አዕምሮዬ በተለያዩ ኃሳቦች ተወጥሮ የሰነበተውን ያህል፣ ሰሞኑን ግን ግንዛቤ እየወሰድሁ አደብ ገዝቼ ማንበብ በመቻሌ፣ እዚህ መግባቴ ለበጎ ይሆን? በማለት ለራሴ ሞራል ሰጠሁት።

# እኛ እንዲህ እንላለን (ሁለት)

## የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ማድረግ ከሚገቡን ጉዳዮች ጥቂቶች

በአበባው ይርጋ አዳሙ (ዶ/ር)
ትምህርትና ስነባህርይ ፋኩልቲ

### መግቢያ

እንደምን ከረማችሁ? ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ካመጣቸው አዎንታዊ ለውጦች አንዱ ከስብሰባና ከሻይ ቡና መድረክ ባለፈ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተለያዩ ገንቢ ሃሳቦችን፣ ትዝብቶችንና መልዕክቶችን የሚያስተላልፍበት፣ የሚያነብበትና የሚያቀርብበት አማራጭ መድረክ ማቅረቡ ነው፤ አማራጩን መጠቀም ደግሞ የማህበረሰቡ ፋንታ ነው። እኛ ይህን ዕድል ተጠቅመን ዛሬ እንዲህ እንላለን።

አንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ጥሩ የሚለውን ሃሳብ ሌሎች እንዲቀበሉት፣ ተቀብለውትም እንዲተገብሩት ወይም እንዲከተሉት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ግለሰቡ/ተቋሙ ትክክል ነው ብሎ ካመነበት የሚያነሳው ሃሳብ ምንም ይሁን ምን ለተፈጻሚነቱ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህ በራሱ ስህተት ላይባል ይችላል። ስህተት የሚሆነው ይህንን ሃሳብ የሚተቹ ወይም ሌላ አማራጭ ሃሳብ የሚያቀርቡትን በደምሳሳው ስም አጥፊ፣ ለውጥ የማይፈልጉ፣ ርዕይ የሌላቸው፣ ጨለምተኞች ወይም ጎታቾች ብሎ ማሰብ ወይም መፈረጅ ነው። በየትኛውም ስሌት የሌላኛውን ወገን ሃሳብ ማዳመጥ እጅግ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም በአንድ ወገን ያለን ታሪክ (one side story) ብቻ ማድመጥና በዚያ ብቻ መመራት ውጤታማ አያደርግም። ስለሆነም በዚህ ጽሁፍ የምናቀርበው ሃሳብ እንደ አንድ የዩኒቨርሲቲው ማህብረሰብ የራሳችንን እይታ ነውና በዚህ መነጽር ብቻ ይታይልን። ይህን ስናደርግም የሌላ ወገን ታሪክ አቅርበንና ሃሳብ አፋጭተን የተሻለ ሃሳብና አካሄድ እናመጣለን በሚል እሳቤ እንደሆነ ልብ ይሉዋል። ዳሩ በቅንነት ላሰበው ከዚህ ውጭ ሌላ ምንስ ሊሆን ይችላል?

የዛሬው ጽሁፋችን የሚያተኩረው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በያዝነው ዓመት መጀመሪያ ላይ ‹‹ሰማያዊ መጽሃፍ፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ›› በሚል መጠሪያ ለህትመት ያበቃት መጽሄት ካነሳቻቸው በርካታ ቁም ነገሮች መካከል አንዱ በሆነው ምርምር ላይ ነው። በሃገራችን በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ የተቋቋሙት የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሙሉ በመርህ ደረጃ በመማር-ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ይጠበቃል። ነገር ግን በበርካታ የትምህርት ተቋማት እንዳየነውና በራሳችን ዩኒቨርሲቲም ኖረንበት እንዳስተዋልነው ከሶስቱ መማር-ማስተማር የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ብቻ ሳይሆን የተቋማቱ ብቸኛ ተልዕኮ እስኪመስል ድረስ ለበርካታ ዓመታት ሙሉ ጊዜና ሀብት ሲፈስበት ተመልክተናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ቢያንስ በዩኒቨርሲቲያችን የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎትም ከፍተኛ ትኩረት ሲሰጣቸውና ለክንውናቸውም ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲደረግ አይተናል፤ ብዙዎቻችንም ተሳትፈናል። ዩኒቨርሲቲው ለእነዚህ አቅጣጫዎች ትኩረት በመስጠቱ ደስ እያለን ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ለለፉት ሁሉ መልካም አድርገዋልና ምስጋና ይገባቸዋል።

የሰማያዊ መጽሐፍ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያነሳቸው ሃሳቦች አንዱ ዩኒቨርሲቲያችን በምርምር ረገድ ለሀገሪቱ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ከፍ ስለማድረግና ይህንንም ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ ፍላጎቶችን እንዴት ማሟላት እንደሚቻል ነው። የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማም በሰማያዊ መጽሐፍ ውስጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲን ከመፍጠር ጋር በተያያዘ የተያዘውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለመተግበር ተግዳሮት ሊሆኑ ይችላሉ የምንላቸውን ሃሳቦች በማቅረብ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲወያይባቸውና የመፍትሔ ሃሳቦችን እንዲያቀርብባቸው ማድረግ ነው። ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው ዩኒቨርሲቲው በምርምር መስኩ ያሰበውን ያህል መጓዝ ይችል ዘንድ ሊያሻሽል ይገባዋል ተብለው የሚታሰቡ ሃሳቦችን ማንሳትና መወያየት ተገቢ ነውና እኛ እንዲህ እንላለን።

### ምቹ የስራ ቦታ መፍጠር አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል

ጥሩ የምርምር ተቋም ለመገንባት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች አንዱ ምቹ የስራ ቦታ ነው። እዚህ ላይ ምቹ የስራ ቦታ ስንል ባደጉት ሃገራት ያለውን ዓይነት ሳይሆን መሰረታዊ ሊባሉና በሃገራችንና በዩኒቨርሲቲያችን አቅም ሊሟሉ የሚገቡና የሚችሉ ሁኔታዎችን ማለታችንን እንደሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት በሀገራችን ውስጥ በአስገራሚ ሁኔታ ተስፋፍቷል። ይህን ተከትሎ ነባር የሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎችም የቅበላ አቅማቸውን ለመጨመር የሚያስችላቸውን መሰረታዊ ጉዳዮች ለማሟላት ላይ ታች ሲሉ አስተውለናል። የመማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤቶች፣ ቤተመጻህፍት፣ የመመገቢያ አዳራሾች፣ ወዘተ በብዛት ተገንብተዋል። ይህ ሲሆን የመምህራንን ብዛትና የቢሮን አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ግንባታ ሲካሄድ ግን አይስተዋልም። ለምን? ለዚህ ዋነኛ ማሳያ ደግሞ በዩኒቨርሲቲያችን በዋናው ግቢና በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ያሉ ቢሮዎች ናቸው። በእነዚህ ግቢዎች ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ ለመምህራን ተብለው የተሰሩ ቢሮዎች ባለመኖራቸው መምህራን ለመማሪያ ክፍል ተብለው በተሰሩ ህንጻዎች እንዲጠቀሙ ተገደዋል። እነዚህ ቢሮዎች በቂ ካለመሆናቸው በላይ የምርምርም ሆነ የማማከር ስራ ለማከናውን ምቹ አይደሉም። ይህ ደግሞ የአደባባይ ሚስጥር ነው። እዚህ ላይ ዩኒቨርሲቲው በምርምር ስራና በስራ ቦታ ምቹነት መካከል ያለውን አዎንታዊ ግንኙነት በሚገባ የተረዳ አይመስለንም። ይህን በተመለከተ የቀረቡ በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎች አሉና እነሱን መመልከት ምናልባት ለአጽንኦት ይጠቅም ይሆናል።

ሌሎች ለምርምር ስራ በጣም አስፈላጊ የሚባሉት በቂና በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ ቤተመጻህፍት፣ የምርምር ላቦራቶሪና የኢንተርኔት አገልግሎት ናቸው። እነዚህም አሁን ያሉበት ሁኔታ የታሰበውን ተቋም ለመገንባት በቂ አይደሉምና መላ ሊባሉ ይገባል። በአጠቃላይ ጥሩ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመፍጠርና ነገራችን ‹‹እቅድ ዶሮ ክንውን ሽሮ›› እንዲሉ እንዳይሆን ለምርምር ስራ አስፈላጊ ለሆኑት የመምህራን/የተመራማሪዎች ቢሮ፣ ቤተመጻህፍት፣ የምርምር ላቦራቶሪና የኢንተርኔት አገልግሎት አጽንኦት በመስጠት ማሻሻል ተገቢ ነው እንላለን።

### በምርምር ውጤት የሚቃኝ አሰራርን ማዳበር ተገቢ ነው

ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን ዓላማው የምርምር ስራዎች መፍለቂያ ብቻ ሆኖ መቀጠል ሳይሆን በምርምር ስራዎች ውጤት አምኖ የአሰራር አቅጣጫውን ማሻሻል ጭምር መሆን አለበት። እኛ እስከምናውቀው ድረስ ዩኒቨርሲቲውም ሆነ ተመራማሪዎች ለዚህ ዝግጁ አይደሉም። የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፎችን ጨምሮ በዩኒቨርሲቲውና በሌሎች ድርጅቶች የገንዘብ ድጎማ የተሰሩና ትኩረታቸውን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ላይ ያደረጉ በርካታ የምርምር ስራዎች አሉ። የእነዚህ የምርምር ውጤቶች ምን ይላሉ ብሎ የሚጠይቅ የዩኒቨርሲቲ አካል የለም። ተመራማሪዎችም የመጨረሻ ግባቸው የምርምር ስራውን መጨረስ ከተቻለም ማሳተም እንጂ የምርምር ስራው በሚያሳየው ውጤት መሰረት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ አስፈላጊውን ጥረት ሲያደርጉ አይስተዋልም። ከምርምር ዋነኛ ዓላማዎች መካከል ለሀገርና ለማህበረሰብ ጠቃሚ የሆነ አዲስ ነገር መፍጠርና የተለያዩ አሰራሮችን በማሻሻል ህብረተሰቡን የመልካም ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ተጠቃሽ ናቸው። አንድ የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን የሚሻ ተቋም ደግሞ እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮች ወደ ጎን ሊተው አይገባምና የምርምር ውጤቶችን እያደነ አስፈላጊ ከሆነ በጥልቀትና በስፋት ደግሞ እያስጠና አሰራሩን ማሻሻልና የምርምር ውጤት ተጠቃሚ በመሆን የምርምር ውጤትን ጠቀሜታ በማሳየት አርዓያ መሆን ይገባዋል። የራሱን በምርምር ውጤቶች ሳይቃኝ ለሌሎች ተጠቃሚ ሁኑ ማለት ምን ለራሱ አያውቅም እንዲሉ ነው።

### የምርምር ስራዎችን መሰብሰብና መጠቀም

በተለያዩ መድረኮች ላይ ለመጠቆም እንደሞከርነው የተለያዩ መጽሃፍትና የምርምር ጆርናሎች እምብዛም ባልተሟሉበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ለማስተርስና ለዶክትሬት ዲግሪ ሟሟያነት የሚያቀርቧቸው ቴሲሶች የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና መምህራን ለሚያደርጓቸው የምርምር ስራዎች እጅግ በጣም ጠቃሚ ናቸው። እንዴት ብለን የጠየቅን እንደሆነ አንደኛ ዩኒቨርሲቲው ያለበትን የመጽሃፍትና የምርምር ጆርናሎች እጥረት በመቅረፍ ረገድ በተወሰነ መልኩ ያግዛል፤ ሁለተኛ ማን ስለምን አጠና የሚለውን እንድናውቅ ስለሚያስችል በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ጥናት ማድረግ የሚፈልግ ባለሙያ የጥናቱን ባለቤት በማግኘት ስለጉዳዩ የበለጠ ለማወቅ ወይም ቀጣይ የምርምር ስራዎችን በትብብር ለመስራት ዕድል ይሰጣል። ሶስተኛ እነዚህን የምርምር ስራዎች ማንበብ ደግሞ ለምርምር የሚሆኑ ሌሎች አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን ለማፍለቅ ያግዘናል። የአፈጻጸም ሂደቱን ለዩኒቨርሲቲው ብንተውም እኛ ግን እንዲህ ቢሆን መልካም ነው እንላለን። ትምህርታቸውን በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የተከታተሉ/የሚከታተሉ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ቴሲሳቸውን ለዩኒቨርሲቲው

> በራሳችን ዩኒቨርሲቲም ኖረንበት እንዳስተዋልነው ከሶስቱ መማር-ማስተማር የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ብቻ ሳይሆን የተቋማቱ ብቸኛ ተልዕኮ እስኪመስል ድረስ ለበርካታ ዓመታት ሙሉ ጊዜና ሀብት ሲፈስበት ተመልክተናል።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# “እኔ የተነሳሁት ማሕበረሰቡን ለመጥቀም ነው::”

ዶክተር ንብረት አስራደ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ ለማሳካት በምርምርና እዉቀት እንዲሁም በማህበረሰቡ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል። ጉደለት የሚታይባቸውን መርጦና ቅደም ተከተል አውጥቶ፣ የትኩረት አቅጣጫ በመለየት ባልተበታተነና ዘላቂነት ባለዉ ሁኔታ የስልጠና፣ የማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል። ማህበረሰቡ የሚያስፈልጉትን ቴክኖሎጂዎች ከተገቢው ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ጋር እንዲጨብጥ እንዲሁም ተፈጥሮን በመጠበቅ በዘለቄታዊነት ህይወቱን እንዲቀይር ማብቃት የጽ/ቤቱ ዋና አላማ ነው። በጽ/ቤቱ ከተሰሩት የማህበረሰብ አገልግሎቶች መካከል በደንገል ተክል ላይ የተሰራው ፕሮጀክት አንዱ ነው። ፕሮጀክቱን አስመልክቶ የፕሮጀክቱን አስተባባሪ ዶ/ር ንብረት አስራደ የናይል ጋዜጣ ዘጋቢ አነጋግራቸዋለች። ቃለ መጠይቁን እንሆ!

ናይል፡- በመጀመሪያ ስም እና ኃላፊነትዎን ቢገልፁልን?

ዶ/ር ንብረት፡- ስሜ ዶክተር ንብረት አስራደ ይባላል። በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንግሊዝኛ ዲፖርትመንት መምህር ነኝ።

ናይል፡- በደንገል ፕሮጀክት ላይ ያለዎት ሀላፊነት ምንድን ነው?

ዶ/ር ንብረት፡- በመጀመሪያ የፕሮጀክቱን ሀሳብ ያመጣሁት እኔ ነኝ። በፕሮጀክቱ ውስጥ ያለኝ ሀላፊነት የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ነኝ። ፕሮጀክቱ የተጀመረው በ1998 ዓ.ም ነበር። ከስምንት አመት በኋላ የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰቡ አገልግሎት ሲጠናከር ፕሮጀክቱን እንደገና በመንደፍና አማካሪዎችን በማካተት የተጀመረ ሲሆን እኔም ሀሳቡን ስላመነጨሁ፣ ፕሮጀክቱን በመጀመሪያ ያመንኩበትም እኔ በመሆኔ እና ሀሳቡን ያውቀዋል ብለው ስላሰቡ እስካሁን ፕሮጀክቱን በማስተባበር ላይ ነኝ። በውስጡ ስምንት ሰዎች ተሳትፈዋል።

ናይል፡- ፕሮጀክቱን ለመስራት ምን አነሳሳዎት?

ዶ/ር ንብረት፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከመግባቴ በፊት ያደኩበት ጣና ዙሪያ ቁንዝላ የሚባል አካባቢ ነበር። አካባቢውን በቅርብ ስለማውቀው በአካባቢ ያለውን ደንገል ገበሬው በገፍ ይጨፈጭፈዋል። ከዚያም ወደ አዲስ አበባና ጐንደር ጨፌው ተጭኖ ይሄዳል። ይህ ሲሆን ደንገል በቅርብ ቀን አደጋ ላይ እንደሚወድቅ በመስጋትና ደንገል የሚባል ተክል ‘ነበር’ እንዳይባል በማሰብ እንዴት መታደግ እችላለሁ የሚል ሀሳብ በአዕምሮዬ ሲውጠነጠን ቆይቷል። ሰዎች ከየግቢያቸው ተክለውት ሳይ ለካ ከጣና ውጭ ደንገል መብቀል እንደሚችል ተገነዘብኩ። በተጨማሪም ተክሉ የሳሙና እጣቢም ሆነ የወጥ እጣቢ ቢደፋበት እንደሚስማማው ተረዳሁ። በመሆኑም ፔዳ በር ላይ ካለው ድልድይ ደንገል ቢተከል ሽታው ሊጠፋ ይችላል ብዬ ወደ ቤቴ በመሄድ ፕሮፖዛል አዘጋጀሁ። በቀላሉ የደንገል ተክል ማደጉን ስላየሁና ቆሻሻም እንደሚያጠፋ ስለተረዳሁ ፕሮጀክቱን ማጠናከር እንዳለብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ። ደንገልን ጣና አካባቢ ሰው በቀላሉ ሊቆርጠው ይችላል በማለት ፔዳ ቢገባ ማንም የሚቆርጠው ስለሌለ በግላችን ወደ ፔዳ አምጥተን ተክለነዋል።

ናይል፡- የፕሮጀክቱ አላማ ምንድን ነው?

ዶ/ር ንብረት፡- ፕሮጀክቱ ሶስት ዓላማዎች አሉት። በመጀመሪያ ቆሻሻን ማስወገድ ይጠቅማል። ግንዱን በመጠቀምና በማዘጋጀት ለሰፌድ፣ ለዘንቢል፣ ለምንጣፍ እና ለህፃን መኝታ ይሰራበታል። ለዚህም ወጣቶች ስራ ፈጣሪ ሆነው እንዲሰሩ ይረዳል። ለወጣቱ የስራ እድል ይፈጥራል። ለከተማው ውበት ያመጣል ብለን ነው የጀመርነው። ደንገሉ ቆሻሻውን ለምግብነት በመጠቀሙ ምክንያት በሚተከልበት አካባቢ የሚፈስ ውሃን ያጠራል። የውሃውን የኦክስጅን መጠን /Oxygen level/ ይጨምረዋል። ውሃው ላይ አሳ ይረባል። አሳ እንዲረባ ከተፈለገ የደንገል ተክል መትከል ወሳኝ ነው። በተጨማሪ ደንገል በስሩ ደለልን ለመከላከል ይጠቅማል። ለምሳሌ ቆጋ ሀይቅ ላይ ደንገልን በመትከል ደለልን መከላከል ተችሏል። ንፁህ ውሀ ይጠጣል። የሀይቁ እድሜ በእጥፍ ያድጋል። አሁን ቁጥር አንድ አድርገን እየተንቀሳቀስንበት ያለው ጉዳይ ደለልን መከላከያ አድርጐ ለመስራት ነው።



ዶ/ር ንብረት አስራደ በፔዳ ግቢ በሚገኝ ድልድይ ውስጥ በተከሉት የደንግል ተክል በከፊል

ናይል፡- የደንገል ተክሉ አሁን ያለበት ደረጃ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ወሰደበት?

ዶ/ር ንብረት፡- ተከላ የተጀመረ የካቲት 17/2006 ዓ.ም. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት በተገኙበት የተጀመረ ሲሆን አንድ አመት አልፎታል።

ናይል ጋዜጣ፡- ፕሮጀክቱ ያስገኘው ውጤት ካለ?

ዶ/ር ንብረት፡- ፕሮጀክቱ በተጨባጭ የሚታይ ውጤት አስገኝቷል። ያስገኘውን ውጤት ስናይ ለምሳሌ ድልድዩ ላይ ቆሞ ወይም ሲያልፍ ሽተተኝ የሚል ሰው አይገኝም። በተለያዩ አካባቢዎችና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተተከሉትን የደንገል ተክሎች ማየት ይቻላል። የስራ እድል በመፍጠር ማሕበረሰቡን ማገልገል ተችሏል።

ናይል፡- በቀጣይ ልትሰሩት ያሰባችሁት ምንድን ነው?

ዶ/ር ንብረት፡- ይህን ፕሮጀክት ልክ እንደኮብል ስቶን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ በተለይ ከበላይ ዘለቀ ቀበሌ ጋር በመነጋገር ወጣቱን በማደራጀት እንዲሰራ ታስቧል። የደንገል ተክል አካባቢውን እንዲያስውብና ደንገል የተተከለበትን አካባቢ ስሩ ውሃ የመያዝ አቅም ስላለው ንጥረ ነገሮችን ሳይቀር በመምጠጥ ለምግብነት ያውላቸዋል። ስለዚህ መንግስት ጠቀሜታውን አይቶ በአገር አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ ይወስደዋል ብለን እናስባለን።

ናይል፡- ለዩኒቨርሲቲውም ሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?

ዶ/ር ንብረት፡- ማህበረሰቡ የደንገል ተክልን ፍል ወስዶ በየቤቱ ቢተክለው ተጠቃሚ ይሆናል። እኔ የተነሳሁት ማሕበረሰቡን ለመጥቀም ነው። ከዛም በኋላ ማሕበረሰቡ እኔን ይጠቅመኛል። ከዚህ ፕሮጀክት ያገኘሁት ጥቅም የትምህርት ክፍሌ ለፕሮጀክቱ ጊዜ እንድሰጥ የስራ ጫና በመቀነስ ረድቶኛል። አንዳንድ ጥቅማ ጥቅም ዩኒቨርሲቲው አድርጐልኛል። ስጥ ይሰጥሀል በሚለው መርህ ነው እኔ የማምነው።

ናይል፡- አመሰግናለሁ።

# የደንገል መልሶ ማልማት፣ መጠበቅና መጠቀም ፕሮጀክት ስኬቶች














# እኛ እንዲህ እንላለን ...

ከገጽ 7 የዞረ

እንዲያስረክቡ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በዩኒቨርሲቲው ከመቀጠራቸው በፊት የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ያጠናቀቁ መምህራንም ቢሆኑ በቅጥር ወቅት እንዲያቀርቡ ከሚጠየቋቸው ማስረጃዎች አንዱ ቴሲሳቸው ቢሆን መልካም ነው። ይህ ቢደረግ ዩኒቨርሲቲያችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ለምርምር ስራ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ አጋዥ ስራዎች ባለቤት ይሆናል እንላለን።

## ምን ታውቃለህ እንጂ ማንን ታውቃለህ መንገስ የለበትም

አንድን ስራ በብቃት ለመወጣትና የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ስራና ሰሪ ሊገናኙ ግድ ይላል። በሃገራችንም ሆነ በበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ እንደሚስተዋለው አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ከምን ታውቃለህ ይልቅ ማንን ታውቃለህ›› እየገነነና የተቋማት የአሰራር ስርዓት አካል እየሆነ መጥቷል። እኛም በድፍረት ዩኒቨርሲቲያችን ከመሰል ጉዳይ የጸዳ ነው ማለት አንችልም። ምክንያቱም በአንዳንድ አሰራሮች ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው ለግለሰቡ እንጂ ግለሰቡ ስላለው ዕውቀትና በዕውቀቱ ለሚፈለገው ስራ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ሳይሆን ሲቀር እናስተውላለን። እዚህ ላይ ‹‹ምን ታውቃለህ›› አንድ ሰው ስላለው እውቀትና ክህሎት የሚመለከት ሲሆን ‹‹ማንን ታውቃለህ›› ደግሞ ከግለሰቡ ዕውቀትና ክህሎት ይልቅ በጓደኝነት፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ ወዘተ ያለን ቅርበት መሰረት ባደረገ መልኩ የሚሰሩ ስራዎችን ይመለከታል። የ‹‹ማንን ታውቃለህ›› አካሄድ እጅግ አደገኛና በሚገነባው ‹‹የራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ›› ላይ እየተደነቀረ በተፈለገው ፍጥነትና ጥራት ወደፊት እንዳንሄድ የሚያደርገን መጥፎ እንቅፋት ነው። እንዴት? ብለን ከጠየቅን መልሱ እንዲህ ነው። ሀ) ከምንም በላይ ስራዎች በተሻለ ባለሙያ እንዳይሰሩ ያደርጋል፤ ለ) በሚፈለገው የስራ መስክ (ምርምር፣ ማስተማር፣ አመራር) የተሻሉ ባለሙያዎች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት ይሆናል፤ ሐ) ተማሪዎች ከሚማሩትና ከሚያገኙት እውቀት ይልቅ በየትኛውም መንገድና በምንም ውጤት ተመርቀው ያለበቂ ዕውቀት ስራን በድፍረት እንዲሰሩ ያደርጋል፤ ይህም የትምህርትን/እውቀትን አስፈላጊነት ያራክሳል፤ መ) ዕውቀት የሌላቸው ሰዎችን ለኃላፊነት ይጋብዛል። ይህም ብቃት ያላቸው ሰዎችን የስራ ተነሳሽነት ያሚሸሻል። የእነዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ባለህበት ሂድ ወይም ውድቀት ነው።

በአጠቃላይ ዕውቀትና ክህሎት ከፍተኛ መመዘኛ በሆኑበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ከ‹‹ምን ታውቃለህ›› ይልቅ ‹‹ማንን ታውቃለህ›› የሚል አሰራር ከነገሰ በእውቀታቸው የተሻለ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሰዎች እንዲዋጡና በአሰራሩ ተስፋ እንዲቆርጡ ያደርጋል። ከጊዜ ብዛት እነሱም ካላቸው ዕውቀትና ክህሎት ይልቅ ሰዎች በተለያየ መልኩ እንዲያውቋቸው ጥረት እንዲያደርጉ ያስገድዳል። ይህን ማድረግ ህሊናቸው የማይፈቅድላቸውና በስራቸው ብቻ እንዲያገለገሉ፣ እንዲታወቁና እንዲዳኙ የሚፈልጉት ግን ምርጫቸው ሌላ ይሆናል - ዩኒቨርሲቲውን መልቀቅ። ስለሆነም በሰማያዊ መጽሃፍ ላይ የተጠቀሰውን ምርጥ ተመራማሪዎችና አስተማሪዎች የሞሉበት ተቋምን ስንፈጥር እንደወንዝ ውሃ የሰማው እየሄደ ያልሰማው የሚመጣበት ተቋም እንዳይሆን የ‹‹ምን ታውቃለህ›› እንጂ የ‹‹ማንን ታውቃለህ›› አሰራር መንገስ የለበትም እንላለን።

## እኔ ምናገባኝ ማለት የለብንም

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በርካታ መልካም ስራዎችና ኃላፊዎች እንዳሉ ሁሉ በርካታ መልካም ያልሆኑ ስራዎችና ኃላፊዎችም አሉ። እኛ እንደታዘብናው አብዛኛዎቻችን የዩኒቨርሲቲ መምህራን/ተመራማሪዎች ብልሹ የምንላቸውን አሰራሮችም ሆነ እንዲህ አይነት አሰራር እንዲሰፍን ምክንያት የሆኑ ግለሰቦችን በሻይ ቡናና በየቢሮው ኮሪደር ስንተች እንስተዋላለን። ነገር ግን እንዲህ አይነት ስራ የሚሰሩትንም ሆነ አሰራሩን በተመለከተ ከሚመለከተው ክፍል ጋር ስንወያይ ወይም ስራውን ሲያደናቅፍ ያየነውን ግለሰብ ስንመክርና ስንተች አንስተዋልም። እንዲህ እንዳናደርግ ከሚያደርጉን ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ‹‹ምናገባኝ›› የሚል ክፉ ደዌ ነው። ለዚህ ክፉ ደዌ መንስዔዎቹ ደግሞ ቀደም ሲል ስንሰጣቸው የነበሩ ገንቢ አስተያየቶች አንድም ከዚህ ግባ የሚላቸው አጥተው አንድም በአሉታዊ አሳቢነት አስፈርጀውን ሊሆን ይችላል። ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ብዙዎቻችን አካዳሚያዊ አውድን ከማህበራዊ አውድ ለይተን ስለማናይ ስህተት የሚሰሩ ሰዎችን አንተችም። መልካም ያልሆኑ አሰራሮችንና ሰሪዎቻቸውን እያየን ‹‹ምናገባኝ›› የምንል ከሆነ ይህ ተቋም ለእኛ አይነቱ አልተዘጋጀምና በጊዜ ቦታችንን መፈለግ አለብን። በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ውስጥ የምንሰራ ምሁራን በሙሉ ምሁራዊ ሃላፊነት፣ ሐቀኝነትና የያገባኛል ስሜት (Intellectual integrity) ሊኖረን ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ሰው ከስህተቱ ተምሮ የሚሻሻልበትን እንዲሁም መልካም አሰራር የሚሰፍንበት አጋጣሚዎችና አካሄዶች በመድፈን እንተባበራለን፤ አሰራሩን እናማርራለን፤ ግለሰቦችን እናማለን። ልናውቅ የሚገባን ጉዳይ ተገቢ ያልሆኑ አካሄዶችና አሰራሮችን የመታገልና የመለወጥ ኃላፊነት የጥቂቶች ብቻ አለመሆኑን ነው። በዩኒቨርሲቲው ጉዳይ አንተም፣ አንቺም፣ እኛም ያገባናል። ምርጫችን ከዚህ በታች በቀረበው ግጥም ውስጥ የቀረበው ሃሳብ ከሆነ ግን እየሰራን ያለነው በትክክለኛ ቦታ እኛ እውን ምሁር ነን ወይ ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል።

### እኔ ምን አገባኝ

እኔ ምን አገባኝ የምትሉት ሃረግ
እሱ ነው ሀገሬን ያረዳት እንደበግ
የሚል ግጥም ልጽፍ ብድግ አልኩኝና
ምን አገባኝ ብዬ ቁጭ አልኩ እንደገና
(ኑረዲን ኢሳ፣ 2000)

## ‹‹በመሰለኝና በደሳለኝ›› መስራት አንድ ሊባል ይገባል

በቅድሚያ ይህችን ‹‹በመሰለኝና በደሳለኝ›› የምትል ሃሳብ ‹‹ቤቶች›› ከሚል ተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ እንደወሰድናት እወቁልን። ይህችን አባባል በዚህ ጽሁፍ ማንሳት የወደድነው አባባሏን ለማስተዋወቅ ሳይሆን ሃሳቧ የያዘችው ቁምነገር በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ሲተገበር ስላየን ግራ እጃችንን ጨብጠንና ከፍ አድርገን እንዲህ ዓይነት አካሄድ ይቅር ብለን ድምጽ ልናሰማ ነው። ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት አዋጅ በተጨማሪ የተለያዩ ተግባራትን በስርዓትና በመመሪያ መሰረት ለመተግበር የሚያስችለው የመተዳደሪያ ደንብ (ሌጂስሌሽን) አለው። አካሄዱ ይህ ቢሆንም አንዳንድ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ኃላፊዎች ይህንን ዘንግተው አንዳንዴም ተጠያቂነት ጠፍቶ ‹‹በመሰለኝና በደሳለኝ›› ሲሰሩ ይስተዋላል። ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚሰጡት ዲፕሎማ ሁሉ ኃላፊነትም የሚሰጠው ‹‹ከነሙሉ ጥቅሙ፣ ክበሩና ግዴታው›› ይመስለናል። ሁሉም ኃላፊዎቻችን ጥቅሙና ክብሩን በሚገባ የሚያውቁት ሲሆን ግዴታውንና ከዚያ ጋር የሚያያዘውን ተጠያቂነት ግን ሲረሱ ወይም በማን አለብኝነት ሲጥሱ ይስተዋላል። እንዲህ አይነት ተግባር ደግሞ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመሆን ዓላማ ላነገበ ተቋም አሜኬላ ናቸው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ደግሞ በአንድ ዩኒቨርሲቲ፣ በአንድ የመተዳደሪያ ደንብ የሚመሩ ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች ለተመሳሳይ ጉዳዮች የተለያዩ ምላሾችን መስጠታቸው ነው። ይህን የምንለው ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች የተሰጣቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ተጠቅመው የሚወስኗቸውን ውሳኔዎች ሳይሆን በመመሪያ የተቀመጡ ጉዳዮችንና ልዩነት ሊታይባቸው የማይገባውን ነው። እንዲህ አይነቱ ‹‹የመሰለኝና የደሳለኝ›› አሰራር የመርህ ጥሰት ከመሆን ባሻገር የመልካም አስተዳደር እጦትን ስለሚያሰፍን አሉታዊ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው።

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር እናንሳ። ብቁ ተመራማሪዎችን ለማፍራት ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ለተመራማሪዎች እውቅናና ማበረታቻ መስጠት ተጠቃሽ ናቸው። እውቅናና ማበረታቻዎችም በተለያየ መልኩ ሊሰጡ ይችላሉ። ዩኒቨርሲቲው በዚህ ረገድ ጥሩ የሚባሉ ተግባራትን በተለያየ መልኩ ሲያከናውን አይተናል። ‹‹የራዕይ ጥበብ 2017 መንገድ›› ለተሳፋሪዎቹ ምቹ እንዲሆኑ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል ይህ አንዱ ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል። ነገር ግን አንዳንድ እውቅና አሰጣጦች ግራ የሚያጋቡና ተጠየቃዊነት የጎደላቸው ከመሆናቸው የተነሳ የአንድን ወገን የስራ ተነሳሽነት የሚጎዱ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲው እውቅና ከሚሰጥባቸው መንገዶች አንዱ መምህራን ካሉበት ደረጃ ወደ ሌላ ከፍተኛ ደረጃ ሲያድጉ (ረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ) ስማቸውንና የደረጃ ዕድገቱን ዓይነት በመግለጽ (የምርምር ስራዎች ዝርዝር እንደማይቀርቡ ማስታወስ ያስፈልጋል?) በማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ መለጠፍ ነው። ይህ የሚደረገው ግን የሚሰጠው ዕድገት መምህሩ ባሳተመው የምርምር ስራ ወይም አጋዥ የማስተማሪያ መጽሃፍ ሲሆን ነው። ሶስት ወይም አራት ወይም አምስት ዓመት ተምሮና የምርምር ስራ አካሂዶ በሚያገኘው የፒኤችዲ ዲግሪ የደረጃ ዕድገት የሚሰጠው መምህር ግን ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ለሚያድገው መምህር በሚደረገው መልኩ ዕውቅና አይሰጠውም። ይህ ለምን ሆነ ብሎ ለሚጠይቅ በቂ ምላሽ የለም፤ ምክንያቱም አሰራሩ ‹‹በመሰለኝና በደሳለኝ›› እንጂ ተጠየቃዊ ባለመሆኑ። ይህ ዓይነቱ ከፋፋይ አሰራር ለፒኤችዲ ዲግሪና በእዚያ የሚገኝን ዕድገት የሚያጣጥል ስለሚሆን ሊስተካከል ይገባዋል። በአጠቃላይ የተሻለ የምርምር ተቋም ለመሆን እነዚህና በዚህ ጽሁፍ ያልተጠቀሱ በርካታ ምክንያታዊ ያልሆኑና መመሪያን ያልተከተሉ ‹‹የመሰለኝና የደሳለኝ›› አሰራሮች ሊታረሙ ይገባል።

በአጠቃላይ ወደምናልመው የምርምር ተቋም ለመድረስ የምናደርገው ጉዞ አንድም ዘዋሪዎቹ ብቃት ያነሳቸው ሆነው፣ አንድም ቅርብ ወራጅ ብቻ ተሳፍሮ፣ አንድም ተመራማሪዎች የተሳፈሩባቸው መኪናዎች የተቀቡት ቀለም እንጂ ሞተራቸው አሮጌ ሆኖ፣ አንድም በቂ ነዳጅ ሳይዙ ሆኖ እንዳይደናቀፍ አደራ እንላለን። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከወዲሁ በጥሩ ተሽከርካሪዎች፣ በጥሩ ዘዋሪዎች፣ በቂ ነዳጅ ሞልቶና ዘላቂዎችን ጭኖ መጓዝ ተገቢ ነው። ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ በተቻለ መጠን ነባራዊ እውነታዎችን በመቀበል፣ አላስፈላጊ አሰራሮችን እንዲታረሙ በመጠቆምና ተቋማዊ ለውጥን በማስቀደም በግልም ሆነ በቡድን ጥሩ ተመራማሪዎች ለመሆን የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን።

እንዲያው ለውይይት ያህል ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን አነሳን እንጂ ሌሎች ጉዳዮችንም በመመካከር ማሻሻል አስፈላጊ እንደሆነ እንረዳለን። የእኛ ሃሳብ እኛ እንዲህ ስንል ሌሎችም እንዲያ ይላሉ ብለን እንጂ በዚህ ጽሁፍ ሁሉን አንስተን መወያት አንችልም፤ አናስበውምም።

# ጠለፋ

**በሂሩት አድማሱ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት**

**nanihira@gmail.com**

በጠዋቱ የስልኳ ጥሪ ከእንቅልፏ ስላናጠባት እየተነጫነጨች ስልኳን በዳበሳ አነሳችው::

"ሄሎ"

"ሄሎ ሳምሪ::"

"ማን ልበል?"

የእህቷ እጮኛ ነበር:: በጥብቅ እንደሚልፈጋት ሲገልጽላት የሰማችውን ማመን አቃታት:: እህቷ ሳትሰማት መምጣት እንዳለባት ስለነገራት ደግሞ ይበልጥ ጉዳዩ አሳስቧታል:: ለምን ፈለገኝ? የሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው የፈለጋትን ሰው ስታገኝ ብቻ ነው:: ለእህቴ ልንገራት ወይስ አልንገራት እያለች ጥቂት ካመነታች በኋላ ልብሷን ለባብሳ ቁርሷን እንደነገሩ ቀማምሳ ወደ ቀጠሮው ቦታ አመራች:: ምን እንደሆነ ባታውቅም ውስጧ ግን ድንግጥ ድንግጥ ይልባታል:: የምትረግጠው መሬት ሳታስተውል፣ የምታስበው ሃሳብ ሳትጠልቅ ላይ ላዩን ትጋልብበታለች:: የተባለው ቦታ ደረሰች::

መናፈሻው ጠዋትና የስራ ቀን ስለሆነ ነው መሰል ብዙ ሰው አይታይበትም የቀጠራት ዳንኤል ግን ከጓደኛው ቢኒያም ጋ አንድ ጥግ ተሰይመዋል:: አይኖቿን ከወዲያ ወዲህ ስታማትር አየቻቸው:: ምልክት ሰጧትና ወደተቀመጡበት አቅጣጫ አመራች::

"እንኳን ደህና መጣሽ ሳምሪ::"

"እንኳን ደህና ቆያችሁኝ::" አለች በውስጧ የለምን ተፈለግሁ ጥያቄ እየተመላለሰ::

ዳንኤል ቁጭ እንድትል በሚጋብዝ አኳኋን ተነስቶ አስቀመጣትና ከምን እንደሚጀምር በማሰብ ጥቂት ቆየ:: ጓደኛው ቢኒያም አይዞህ በሚል ጠቅሶ አደፋፈረው:: ለንግግሩ መክፈቻ ይሆን ዘንድ የሚጠጣ ነገር እንድታዝ ጋበዛት:: "ሻይ!" አለች ባትፈልግም ጥያቄውን ለመቀበል ያህል:: ስሜቱን እንደምንም ተቆጣጥሮ ንግግሩን ጀመረ::

"ወደ ጉዳያችን እንግባ ይኸውልሽ ሳምሪ ከእህትሽ ጋር ጋብቻ ለመፈጸም ሽማግሌ ልኬ ተፈቅዶልኝ ነበር:: ይሁን እንጂ በሚገባ ውስጤን ሳጤነው ከሷ ጋር አብሬ እንድኖር የሚያስችል ፍቅር፣ ትዕግስትና ፍላጎት የለኝም::"

የሳምራዊት ልቧ ለሁለት ተሰነጠቀ፤ ድንጋጤዋ ከመጠን ያለፈ ነበር:: አይኖቿ እንባ አቀረሩ ጉሮሮዋ በምሬት ጭስ ሲታፈን ተሰማት እንደምንም ራሷን ገዝታ

"ለምን ከዚህ ሁሉ በኋላ! ለምን? ይህን ለማለት የዘገየህ አይመስልህም?"

"ዘግይቻለሁ! ግን ምንም ቢሆን ወደትክክለኛው አቅጣጫ የሚወስድሽን መንገድ ካልያዝሽ እንደገና ተመልሰሽ ወደ ዋናው መንገድ መግባት አለብሽ:: እና የእኔና የሷ ሕይወት አብሮ የሚዘልቅ አይነት ሆኖ አላገኘሁትም::"

"እንዴት ከዚህ ሁሉ ዝግጅት በኋላ? ምን ምክንያት ተፈጠረ?"

"ይኸውልሽ እህትሽ በቁንጅናዋ እንከን የሚወጣላት አደለችም:: ቁም ነገረኛም ነች:: ግን ሀይል ታበዛለች፤ ነገሮችን እሷ በፈለገችው መንገድ እንጂ በውይይት በጋራ እንድንወስን አትፈልግም! ሁሌ ተናጋሪ እንጂ ሰሚ አይደለችም::"

"አውቃለሁ:: ግን ይህን የተረዳኸው አሁን ነው?"

"ጥቂት ቆይቻለሁ:: እለውጣታለሁ የሚል እምነትም ነበረኝ:: ግን ፈጽሞ የምትበገር አይነት አይደለችም:: በዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ ተነጋግረናል:: በባህሪዋ ትደሰታለች፤ ለመለወጥም አትፈልግም፣ ትክክል ነኝ ብላ ታምናለች:: ይህን ባህሪዋን ተቋቁሞ የሚያኖር ፍቅር ደግሞ የለኝም::እናም የማይጸና ትዳር ከመመስረት ቢቀር ይሻላል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ::"

ሳምራዊት እልህ እየተናነቃት የሰማችው ዜና በእምባ ታጀበ:: ድምጿን አውጥታ ማልቀስ ጀመረች:: "ወይኔ እህቴ ጉድሽን አልሰማሽ፣ ወይኔ እናቴ፤ ያ ሁሉ ልፋትሽ! ምን ሳርግሽ:: ከዚህ አይነት ጉድ ማን ይሆን የሚያወጣሽ:: ከዚህ ሁሉ በኋላ በመጨረሻው ሰዓት ይበላሽ!" እንባዋ በመንታ መስመሮች ይፈስ ጀመር::

"ተረጋጊ እንጂ ሳምሪ አላስጨረስሽኝም እኮ!"

"ምን የቀረህ ነገር አለ? ለቤተ ዘመድ ሁሉ ተነግሮ ካበቃ በኋላ ሀገር ምን ይላል!"

"ምንም አይልም:: ወይም ‹ጉድ አንድ ሰሞን ነው::› ነው የሚባለው ከዚህ የባሰ ነገር ሲመጣ ወይም በጊዜ ሂደት ይረሳል:: ይልቅ አንደኛውም ጉዳይ ስለጨረስኩ ሁለተኛውን ልንገርሽ"

እንባዋን መግታት ተሳናት:: እየተንዘፈዘፈች ራሷን ነቀነቀች:: በዚህ ሰዓት ተጨማሪ ነገር መስማት አልፈለገችም:: ብቻዋን መሆን አምሯታል:: ለቤተሰቦቿ ይህን ጉዳይ እንዴት እንደምታረዳቸው ማሰብ አለባት:: ተጨነቀች:: ለጊዜው ማድረግ የምትችለው ነገር አልመጣላት ስላለ ነገር ሁሉ ዝብርቅርቅ አለባት:: ንጹሕ አይኖቿ ደፈረሱ:: ቀስ በቀስም እየቀሉ መጡ:: ሁሉ ነገሯ ይንቀጠቀጣል:: ይህን ጊዜ ዳንኤል መታገስ አቃተው:: እንባው ቢመጣም እንደምንም ስሜቱን ተቆጣጥሮ እግሮቿ ስር በርከክ አለ::

"ሳምሪ ይቅርታ አድርጊልኝ:: የመጨረሻ ቃሌን ልስጥሽ:: እህትሽን ብተዋትም ለመልካም ነው:: የተደረገውም ዝግጅት ምንም አይሆንም:: አይዞሽ:: አንቺ ብቻ ልብ ብለሽ አድምጪኝ:: ከተግባባን ይህን አሳዛኝ ነገር ወደ ደስታ መለወጥ እንችላለን::"

"የምን መግባባት አመጣህ? እንዴትስ ነው አሳዛኙን ነገር ወደ ደስታ የምንለውጠው?"

"ሳምሪ፣ ካየሁሽ ጀምሮ..."

"ምን?!"

"አዎ ‹ያበጠው ይፈንዳ› ይላል ያገሬ ሰው:: ካየሁሽ ጀምሮ አፍቅሬሻለሁ:: እህትሽ ሚዜዎቿን ያስተዋወቀችኝ ዕለት አንቺም መጥተሽ ነበር:: በቃ የዚያን ቀን እውነት ነው የምልሽ ሁለመናዬ ነው አንቺን የወደደ:: ራሴን ለመገሰጽ እስቤ ሞክሬም ነበር ግን የሆነ ሀይል ሁሉ ነገሬን ሲቆጣጠር ተሰማኝ:: ደስታና ሀዘን ተፈራረቀብኝ:: በዚያን ወቅት እንደዚህ ያሉ ተቃራኒ ስሜቶችን ያስተናገድኩት:: አንድም እንደዚያ ያለ የፍቅር ስሜት የተሰማኝ ከረጅም የጊዜ ቆይታ በኋላ በመሆኑ የፈጠረብኝ ደስታ ከመጠን ያለፈ መሆኑ፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእህትሽ ጋር የጀመርነው ጉዞ ምን የራቀና ያህል እሷን እንደሚጎዳት ሳስብ የተሰማኝ ሀዘን ደግሞ መፍትሔ አልባ ሆኖብኛል::"

የሰማችውን ማመን ያቃታት ሳምራዊት ዳንኤልን ፊት ለፊት መመልከት አልቻለችም:: ምን እንደምታስብም ቸገራት:: ብቻ በደመነፍስ አይኖቿ በሰፊው ተከፍተው ትኩረታቸውን ምንም ላይ ሳያደርጉ ይማትራሉ:: የሚያድን ፍለጋ ይቅበዘበዛሉ::

"ከዚያ ወዲም በተገናኘንባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ሳይሽ ፈገግታሽ፣ ለነገሮች ያለሽ እይታና አረዳድ የጠለቀ ሆኖብኛል:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ህይወትን ቀለል አድርገሽ መመልከትሽና ለዛ ያለው ሳቅሽ ካንቺ ውጪ ሌላ እንዳላስብ አድርጎኛል:: እውነቴን ነው የምልሽ ማርከሽኛል:: ቢኒያምን እዚህ እንዲገኝ ያደረኩት ያለምክንያት አይደለም:: ከመጀመሪያው ቀን አንስቶ የሚሰማኝን ሁሉ ሳልደብቅ ያካፈልኩት ጓደኛዬ ስለሆነ ምስክር ይሆነኛል ብዬ ነው:: አይደል ቢኒ!"

"አዎ! በመጀመሪያ ሲነግረኝ እኔም ደንግጬ ነበር:: ሆኖም ስሜቱ እየጠለቀና ከቀን ወደ ቀን እየጠነከረ ሳየው እውነተኛ ስለሆነ እንዲተወው መምከር አልቻልኩም:: ፍቅር የሁለት ወገን ሀሳብ ነውና ላንቺ መንገሩ አማራጭ ይሆናል ብለን ነው ተወያይተን የጠራንሽ::"

"ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል:: የእህቴ እጮኛ እንዴት እኔን!"

"ይህ የሆነ ነገር ነው ሳምሪ:: ይልቅ ጊዜ አናባክን:: አንቺ እሺ ባትይኝም እህትሽን አላገባትም:: ምክንያቱን ላንቺ የተሰማኝን አይነት ስሜትና ጥልቅ ፍቅር ለሷ አልተሰማኝም:: ስለዚህ ለማሰቢያ ሶስት ቀን ሰጥቼሻለሁ:: እሺ ካልሺኝ ይዜሽ ለተወሰነ ቀን እጠፋለሁ:: ዘመናዊ ጠለፋ እጠልፍሻለሁ:: ከዚያ ሁኔታው ሲረጋጋ ተመልሰን እንመጣለን::"

ፍጹም ግራ ተጋባች እንዴትስ አድርጋ ይህን ሀሳብ ልታስተናግድ እንደምትችል ጨነቃት:: ለብዙ ጊዜ አፍቅራ ተከድታለች:: ህመሙ በጣም ከባድ እንደሆነ ታውቃለች:: በእውነት የሚያፈቅራትን ሰው ፍለጋም ማትራለች:: በአጭሩ ፍቅር የለም ወደሚል ድምዳሜ ደርሳ ነበር:: ግን ባልጠበቀችው አቅጣጫ ፍቅር የልቧን በር አንኳክቶ ክፈችልኝ እያላት ነው:: የመጣበት መንገድ እንጂ የመጣውን ሰው መቀበል አልከበዳትም:: ከእህቷ ይበልጥ የሚማርክ መልክ ባይኖራትም ይህን አይቶ ውስጧን ተረድቶ የሕይወት አጋሯ ሊሆን ምርጫ የሰጣትን ሰው እንደምን እንደምታስተናግደው ጭንቅ አላት:: እህቷ፣ እናቷ፣ አባቷ... ጎረቤት ወዳጅ ዘመድ ምን ይላል? ፈራች:: ሁኔታው ከጠበቀችው በላይ ስለሆነባት ዝምታዋን መረጠች::

"ሳምሪ በቃ አትጨነቂ:: ጊዜ ውሰጅ:: እሺ ብትይኝ ደስታዬ ዳርቻ አይገኝለትም:: አይሆንም ብትይኝ የማደርገውን ባላውቅም ውሳኔሽን አከብራለሁ:: ምክንያቱም ፍቅር በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ነውና የሚሰምረው:: ከሶስት ቀን በኋላ በሃሳቤ ከተስማማሽ እዚሁ መናፈሻ ውስጥ ጠብቂን:: ካልተስማማሽ ግን አጭር የጽሑፍ መልዕክት በስልክ ቁጥሬ ላኪልኝ:: በጣም እወድሻለሁ::"

ምንም ለመናገር አልደፈረችም:: መናፈሻ ውስጥ የነበራቸው ቆይታም በእንዲህ ባለ ሁኔታ ተደመደመ:: ሳምራዊት ወደቤቷ ስትሄድ መሬቱን እግሮቿ ይርገጡ እንጂ ልቧ ከዳንኤል ንግግር ጋር ነበር የቀረው:: ስሜቷን ጥርት ባለ መንገድ መለየት አልቻለችም:: ‹እሺ እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ? እሱስ ታድሏል ጓደኛ አለው ለጓደኛው ሀሳቡን ያጋራል:: እኔን ግን ማን ይረዳኛል? እህቴስ..... ስለሱ እንደነገረችኝ ከሆነ የሚወደድ ሰው ነው:: ግን እሷን ሁልጊዜ ስመክራት እንቢ እያለችኝ ይህ ግትር አመሏ ይኸው ዛሬም እንደተለመደው ፍቅርን ነሳት::› መንገዱ ሀሳቧን ሳትቋጨው አልቆ ቤቷ አደረሳት::

ሶስቱ ቀናት ለሳምራዊት ፈታኝ ነበሩ:: ከዳንኤል ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተያዩበትን ቀን ደጋግማ አሰበች:: በርግጥ እንዳየችው ደንግጣለች:: የሆነ እንግዳ ስሜትም ተሰምቷታል:: ራሷን ገስጻለች:: በዕለቱ ኣይን ለአይን የተያዩ ቀን ጎላ ጎላ ካሉት አይኖቹ የሚወጡት የብርሃን ጨረሮች በቀላሉ የሚረቱ ነበሩ:: የጨበጣት እጁም በቀላሉ አለቀቃትም:: እኔ ነኝ ወይንስ አይኑ ነው ይህን ያህል ሀይል ያለው ብላ አስባለች፤ የጨበጣት እጁ ቶሎ አለመላቀቅ የፈጠረባትን ስሜት ወዲያው እንደምንም ብላ አዳፍናዋለች:: በውስጧ የሚመላለሰውን እንግዳ ሀሳብ ትታ የሚለብሱትን የሚዜ ልብስ የቀለም ምርጫ ላይ የሚከራከሩትን የእህቷ እጮኛና የእህቷ ሚዜዎች ውይይት ሀሳብ በመስጠት ተቀላቀለቻቸው:: በመሀል ይሰነዘሩ የነበሩ ቀልዶች እና ትችቶች ከልቧ ያስቋት ነበር:: በሳቋ ውስጥ የምታገኘው ደስታና እርካታ ብቸኛ መለያዋ ነው ይህን ባህሪዋን ደግሞ ደጋግማ እህቷ ተናግራላታለች:: እሷም ብትሆን ያለገደብ ዘና ባለ መንፈስ በነጻነት ትስቃለች፤ ይሆናል የምትለውን ሀሳብ በድፍረት ትሰነዝራለች::

በትዝታ ባህር ውስጥ ሰጥማ ስለእሱ እና በውስጧ ስለጫረው ፍቅር ስታስብ ደስ እያላት፤ ስለቤተሰቦቿ በተለይም ስለእህቷ ስታስብ እየጨነቃት ድብልቅልቅ ባለ ስሜት ውስጥ ዋዠቀች:: ከእህቷም ሆነ ከእናትና ከአባቷ ጋር ማውራት አስፈራት:: በሁለት ጎራ የሚንጧትን ሀሳቦች በህሊናዋ ሚዛን ላይ አስፍራ መዘነቻቸው:: ውስጧን በሚገባ መረመረችው:: የዳንኤል ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የሷም የልብ ጥያቄ መልስ ያገኘ መሰላት፤ በመጨረሻም ወሰነች::

በሶስተኛው ቀን ሐሙስ ልክ በአራት ሰአት አንድ የእጅ ቦርሳ ብቻ እንዳንጠለጠለች ከመናፈሻው ደረሰች:: ዳንኤልና ቢኒያም የቀደመው ቦታቸው ላይ ተቀምጠው ነበር:: የዳንኤል ፊት በደስታ ፈካ:: ሳምራዊትን ሲያይ ለሷ ምን ያህል ፍቅር እንዳለው ግምቱ ቢጠፋበትም በህይወቱ ሙሉ በሙሉ የተደሰተበት ቅጽበት በመሆኑ አጠገባቸው እስክትደርስ እንኳን መታገስ አልቻለም:: ወደነሱ አቅጣጫ እያመራች ወደነበረችው ሳምራዊት ሮጦ ደርሶ ተጠመጠመባት:: እቅፍ አድርጎ ወደላይ አነሳት:: ከራሱ ትይዩ አድርጎ አሽከረከራት:: ቢኒያምም ደስታውን ተጋራ::

"አመሰግናለሁ ሳምሪ::"

"ቤተሰቦቼን ትቼ፣ ከዘመድ ከወገን ሁሉ ተቆራርጬ ላንተና ለፍቅርህ ብዬ

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

## የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ...

ከገጽ 5 የዞረ

አገልግሎት በመስጠት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው እስካሁን ካሉት የአገር ውስጥ ሆስፒታሎች የተለየ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ታካሚዎች በካርድ ሣይሆን በአሻራ አገልግሎት የሚያገኙበት ስልት ተዘርግቷል፡፡የቀዶ ጥገና ስራ ሲከናወን መረጃው አገር ውስጥም ሆነ አገር ውጭ ካሉ ብቃት ያላቸው የሕክምና ባለሙያዎች ጋር በቀጥታ ትስስር እንዲፈጥር መደረጉ ሆስፒታሉን ከሌሎች ልዩ ያደርገዋል ብለዋል፡፡ የሆስፒታሉ ባለሙያ የአቅም ውስንነት ቢያጋጥመው የተሻለ እውቀት ያለው ሀኪም እንዲያግዘው የሚያደርግ መሣሪያ ሆስፒታሉ ስራ ሲጀምር አገልግሎት ላይ እንደሚውል አስታውቀዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በማብራሪያቸው «የማይሸት ሽንት ቤት መስራት» በሚል መሪ ቃል ደረጃውን የጠበቀና እጅግ ዘመናዊ የሆነ የሀኪሞች መኖሪያ ቤት፣ የተማሪዎች መኝታ ቤት፣ ቤተ-ሙከራ፣ ቤተ መፅሐፍት ወዘተ.... የመሳሰሉት አስፈላጊ ግንባታዎች በግቢው ውስጥ እየተከናወኑ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

ቀጣዩ ጉብኝት ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ማሪታይም አካዳሚ አቅንቶ 18 ሄክታር ላይ ባረፈው የመርከብ ቅርፅ ባለው እና "ድንቅነሽ" ተብሎ በተሰየመው የመርከበኞች ማሰልጠኛ ተቋም ተከናውኗል፡፡

ፕሬዚዳንቱ በዚሁ ወቅት የአካዳሚው ዋና አላማ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙያው ሰልጥነው በውጭ አገር እንዲቀጠሩና የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት እንዲችሉ በመሆኑ አመልክተዋል፡፡ ለዚህ እንዲረዳም ከመርከብ ኩባንያዎች ጋር ግንኙነት መፈጠሩንና በአመት 1000 (አንድ ሺ) ተመራቂዎችን ለማፍራት የተያዘው እቅድ እንዲሳካ ጥረት መደረጉን ገልፀዋል፡፡ ከውጭ አገር የመርከብ ኩባንያዎች ጋር በተፈጠረው ግንኙነት የተቋሙና የሰልጣኞች ተስፋ የለመለመ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል ብለዋል፡፡

ከጉብኝቱ መልስ የሁሉም ዩኒቨርሲቲዎችና የፎረሙ ጽ/ቤት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሄዷል፡፡ የፎረሙ ጽ/ቤት ኃላፊ ፕሮፌሰር ዓቢይ ይግዛው እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ሆነው ልምድ በመለዋወጥ ከመማር ማስተማሩ ባሻገር የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎቶችን ለማከናወን ሁኔታዎችን ያመቻቻል በሚል መሰረታዊ ዓላማ በ2005 ዓ.ም የተቋቋመው ይህ መድረክ ከግብርና፣ ከጤናና ከትምህርት ቢሮዎች ጋር በመነጋገር በክልሉ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ነቅሶ ለማውጣት ስራ በመገፋፋት ሣይሆን በመሣሣብ መስራትን መርሁ አድርጎ ይንቀሳቀሳል፡፡

የፎረሙ ተሳታፊዎች እንደገለፁት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለፎረሙ ቀኝ እጅ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የብቻ ጥረት እሚፈልገውን ለውጥ ማምጣት ያስቸግራል፡፡ ለጋራ አላማዎች ስኬት የጋራ ርብርብ ያስፈልጋል፡፡ በስብሰባው ወቅት የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል፡፡ በተማሪዎች የትብብር መማማር (Collaborative Learning) እና በጣና ውስጥ የተከሰተውን እምቦጭ አረም በተመለከተ የቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፎች በተለይ የተሳታፊዎችን ትኩረት ስበዋል፡፡በቀጣይም ለተሻለ ውጤት ፎረሙ ጠንክሮ መስራት እንዳለበት በዩኒቨርሲቲዎቹ የበላይ አካላት የጋራ አቋም ተወስዷል፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በማሳለፍም ጎንደር ዩኒቨርሲቲን ቀጣዩ የመድረኩ አዘጋጅ እንዲሆን መርጧል፡፡

## ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ...

ከገጽ 4 የዞረ

ገልፀዋል፡፡

ከስልጠናው ተሳታፊዎች መካከል የአካውንቲንግ ተማሪ አባየነሽ ወርቁ እና የስርዓተ ትምህርት ክፍል ተማሪ የሆነው ስዩም ጥላሁን የሕይወት ክህሎት ስልጠናው ወደፊት ራስን እንዴት መምራትና ችግሮችን በቀላሉ እንዴት መፍታት እንደሚችሉ መንገድ ያሳየ እንዲሁም በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው እንዲዘልቁ እገዛ የሚያደርግ መሆኑን ገልፀው ዩኒቨርሲቲው ወደፊትም እንደዚህ አይነት ስልጠናዎችን አጠናክሮ መስጠት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዩኒቨርሲቲው ኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ከዲኬት ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የተቀናጀ የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት እና በኤችአይቪ ኤድስ ዙሪያ የአንድ ቀን ስልጠና ሰጥቷል፡፡

የስልጠናው ዋና ዓላማ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንደሌሎች አቻ ጓደኞቻቸው ለፆታዊ ጥቃትና ለስነ ተዋልዶ መብት ጥሰት ተጋላጭ በመሆናቸው የመከላከል ስልቱን የማሳወቅና ጉዳቱን የመቀነስ ብሎም የተማሪዎቹ የአገለግሎቱ ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው፡፡

በዩኒቨርሲቲው የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክተር ሲስተር ማርታ አስማረ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ስለተዋልዶ ጤናና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያላቸውን የግንዛቤ ውስንነት ጽ/ቤታቸው ተገንበዝቦ ስልጠናውን እንዳዘጋጀው ገልፀዋል፡፡ ተሳታፊዎችም ይህንኑ አውቀው መድረኩን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት አሳስበዋል፡፡ ሰልጣኞቹ በበኩላቸው በዩኒቨርሲቲው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚደረገው ድጋፍ ቀጣይነት እንዲኖረው የዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ በጋራ መስራት እንዳለበት ሐሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

## መፅሐፍ ተመረቀ ...

ከገጽ 5 የዞረ

የመፃህፉ አፃፃፍ ስልቱ ለንባብ የሚጋብዝ እንደሆነም በምሁራኑ ማብራሪያ አጽንኦት ተሰጥቶታል፡፡ በደርግ ሰራዊት አነሳስና ውድቀት ላይ ያተኮረው ይህ መፅሀፍ ከአክሱም ዘመነ መንግስት በመነሳት ስለዘመናዊው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጭምር ተገቢውን መረጃ ይሰጣል፡፡

የሰነድና በሕይወት ያሉ የሰው ማስረጃዎች በመፅሐፍ አባሪ ተደርገዋል፡፡ ተሳታፊ የነበሩት የደርግ ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ የደህንነት አባላት፣ የጦር መኮንኖች ቃል መጠይቆች እንዲሁም በሀገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያተኮሩ ሚስጥራዊ ደብዳቤዎች ተካተውበታል፡፡

## ለአይነ ስውራን ተማሪዎች መሰረታዊ ...

ከገጽ 4 የዞረ

፡ ስልጠናው በቦታ እጥረት፣ የአሰልጣኝ ውስንነትና የቁሳቁስ አለመሟላት እንዲሁም የተማሪዎችን መደበኛ ትምህርት በማይነካ መልኩ ቅዳሜና እሁድ በመስጠት አስፈላጊውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ መቻሉን የዩኒቨርሲቲው አቅም ግንባታ ፕሮግራም ማዕከል ም/ዳይሬክተር አቶ አንዳርጌ ጌራወርቅ ገልፀዋል፡፡ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ስልጠናውን በዋናነት እያገዘ መሆኑንና «Gaws» በተሰኘው ሶፍትዌር በመታገዝ ተማሪዎች ስልጠናውን በሚገባ መከታተላቸውን ተናግረዋል።

የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ አቃቢ ሕግ አቶ አማረ ሲሳይ በስልጠናው ወቅት ተገኝተው እርሳቸውንም ሆነ ሌሎች በርካታ ወንድሞቻቸውን ከአደባባይ እንዳስራቀ በመግለፅ በጥረት ካሰቡት መድረስ እንደሚቻል በአፅንኦት ተናግረዋል፡፡ በስልጠናው የተለያዩ ተለምዷቸውን አካፍለዋል፡፡ አይነስውርነት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ኪቦርድን በሚገባ እንዲያውቁ የሚረዳ በድምፅ በመታገዝ ሁሉን ነገር መስራት የሚያስችላቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ለስልጠናው የተሰጠው ጊዜ ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ለማብቃት ፈታኝ እንደነበር ጠቁመው ተጨማሪ ጊዜ መስጠት እንዳለበትና አይነ ስውራን ተማሪዎች እንደማንኛውም ተማሪ ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ የኮምፒውተር ትምህርት ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል ብለዋል፡፡ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲው የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

## ማህበሩ በዩኒቨርሲቲው ...

ከገጽ 5 የዞረ

እንዲያነሱ ውይይት እንዲካሄድባቸውና ጥናቶች መሬት ወርደው ወደ ተግባር እንደሸጋገሩ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ታስቦ መቋቋሙን ገልፀዋል፡፡ የዘንድሮው የኢትዮጵያ የስነ ሕይወት ባለሙያዎች አመታዊ ኮንፈረንስ ባሕር ዳር ብዙ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ከመሆኗና ለኢኮቱሪዝም ካላት ምቹነት ጋር ተያይዞ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንዲዘጋጅ መደረጉን አመልክተዋል፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ዩኒቨርሲቲው 25ኛ ኮንፈረንሱን ማካሄዱ እንዳስደሰታቸው ገልፀው ዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ መርኃ ግብሮችን እያስፋፋ የምርምር ተቋማትን እያዋቀረ ጥናትና ምርምርን አይነተኛ መገለጫ ለማድረግ ቆርጦ በተነሳበት ወቅት በመዘጋጀቱ የተለየ ግምት እንሰጠዋለን ብለዋል፡፡

በእለቱ የማሕበሩ አባላት የተለያዩ የምርምር ፅሑፎችን ያቀረቡ ሲሆን ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ስነ ሕይወት ባለሙያዎች ማሕበር 26ኛውን ጉባኤ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ቀጠሮ ይዟል፡፡

## ለሬጅስትራር ሠራተኞች ...

ከገጽ 5 የዞረ

ምንነት፣ በፋይል አያያዝና ዘመናዊ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ አስጨብጧል፡፡ መደበኛ ስራዎችን በሚያከናውኑበት ወቅት ወቅት ከተማሪዎች ለሚነሱት የተለያዩ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ይጥሩ እንደነበር ያወሱት ሰልጣኞች መድረኩ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እነዚህን ሌሎች መሰል ተግዳሮቶችን የመለሰ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

ስልጠናው ላይ ከአማራ የስራ አመራር ተቋም ባለሙያዎች ተጋብዘዋል፡፡ በተሻለ አሰራር የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጠን ይበልጥ ለማሳለጥ በተዘጋጀው በዚሁ ሙያዊ የስልጠና ሙድረክ የስራ አመራር ተቋሙን የወከሉት አቶ ታምሩ ተመስገን በጉዳዩ ዙሪያ ሰፊና ተገቢውን ማብራሪያ አድርገዋል፡፡ የተቋሙ አማካሪና የስልጠና ባለሙያው አቶ ታምሩ የአሰራር ስርዓቱን በሰራተኞች ዘንድ ከማስረፅ አኳያ ስልጠናው ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አብራርተዋል፡፡

# የ ግ ጥ ም ጥ ግ

## የለውጥ ሀዋርያ

ፅሁፍ ተለጥፎ አየሁ ካዳራሹ ግድግዳ፣

«የለውጥ ሀዋርያ» የሚል ቀላል መሳይ ዱብ እዳ፡፡

እርግጥ ሀዋርያ ነው የእውቀት አባቱ መምህር፣

ግን የትኛው ሀዋርያ እስኪ መሰረቱ ይመርመር፡፡

በየገጠሩ እየዞረ የፊደል ወንጌል የሚዘራ፣

በአግባቡ የሚያስመርት የእውቀትን አዝመራ፡፡

ከአጥናፍ አጥናፍ እየዞረ ስልጣኔን የሰበከ፣

ጳውሎስ ነው መምህሩ አዕምሮው በብር ያልታወከ?

ነው ወይስ ማቴዎስ ነው፤ የእውቀትን ወንጌል የፃፈ?

ማርቆስ ነው ወይስ ሉቃስ መፅሐፍ ፅፎ ያለፈ?

ስምኦን ነው መምህሩ፤ መስቀል መሸከም ያወቀ፣

ወይስ ዮሐንስ ይሆን እስከፈፃሜው የዘለቀ፡፡

እነዚህን ከሆነ ይሄ ጓዴ መምህር፣

እሰይ እንግዲህ ልኩራ እኔም አገኘሁ ክብር፡፡

ጴጥሮስን የሆነ እንዲሁ ግን ልቡ ለመፍራት የሚዳዳ፣

ዶሮ ከመጮሁ በፊት ሶስት ጊዜ የሚከዳ፡፡

ወይ ይሁዳን ከሆነ ነዋይ የሚያማልለው፣

ለሰላሳ ብር ብሎ ወንድሙን ለሞት የሚተው፣

ይቅርብኝ ሀዋርያነት እኔም ማስተማሬን ልተው፡፡

(የግጥሙ መነሻ ሀሳብ በአንድ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ተለጥፎ የነበረ "መምህሩ የለውጥ ሀዋርያ ነው!" የሚል ጥቅስ ነው፡፡)

አብነት ሰለሞን

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ት/ክፍል መምህር

## ለኬት

ደግነው ተባለ ያለው ላጣ ሲቸር፣

ሲለግስ ተለካ ካለው ሲመነዝር፣፣

የሌለው ደግ ግን ምኑን ለማን ሰጥቶ፣

ደግ እንዴት ይባላል በምን ተለክቶ?

አብነት ሰለሞን

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ት/ክፍል መምህር

## ጠለፋ

ከገጽ 11 የዞረ

መጥቻለሁና አደራ፡፡"

"ግድየለሽም በውሳኔሽ መቼም ቢሆን አትጸጸችም፡፡ ፍቅሬ ፍጹም ነው አይጥልሽም፡፡"

"ከቤተሰቦችሽም ጋር ቢሆን አትቆራረጪም፤ ሽማግሌ እንልካለን፡፡ እንታረቃለን፡፡ እህትሽንም በአስፈላጊው መንገድ እንክሳታለን፡፡ ለሷም ቢሆን ከማያፈቅራት ሰው ጋር መኖር ምን ያደርግላታል? በነገራችን ላይ የምታፈቅረኝም አይመስለኝም፡፡ ለማንኛውም የኔ አበባ አሁን ነገር ሁሉ ከባድ ቢመስልም በጊዜ ሂደት ግን ይስተካከላል፡፡ ጊዜ የማይሽረው የለም ይባል አይደል፡፡

በቃ በስምምነት ጠለፋት ተስማምተው ከተማይቱን ለቀው ሄዱ፡፡ ቢኒያም መኪናውን እያሽከረከረ ሙሽሮች ደግሞ ከኋላ ተቀምጠው እየተጫወቱ በብሩህ ሰማይ ላይ የወጣችው ደማቅ ጸሐይን ከፍቅራቸው ጋር እየሞቁ ወደ ምስራቅ ተጓዙ፡፡

# አራዳ እና ፋራ (ወግ)

ዋለልኝ አየለ (3ኛ ዓመት ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን) 0922341587

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የማንንም ምሁር፣ ፈላስፋ፣ ተመራማሪ ሀሳብ አልጠቀምም፡፡ የግሪክ ፈላስፎችና የዓለም ምሁራን ሀሳብ ሁሉ በዚህ ፅሁፍ ውድቅ ይሆናል (ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል እንዳትሉኝ)፡፡

ቆይ ግን እኔ ፈላስፋ መሆን አልችልም? ደግሞ አንተን ብሎ ፈላስፋ ምን ሰርተህ ነው የሚል ካለ ሙሉ የማዕረግ እድገቴንና ደረጃዬን እነግረዋለሁ፡፡ እንግዲህ ምሁር ነኝና ከትውልዴ ጀምሬ በአጭሩ ራሴን ላስተዋውቅ፡፡ የተወለድኩት ምንም የከተማ ቅልቅል ከሌለበት ንፁሁ የገጠር መንደር ውስጥ ነው፡፡ አስተዳደጌም በዱር በሜዳ ከእኩዮቼ ጋር ከብት በመጠበቅ፣ አባሮሽና ድብብቆሽ በመጫወት ነው፡፡ እድሜዬ ለትምህርት ትንሽ አለፍ እንዳለም የከተማነት ስሜት ከሚሰማት አንዷት የገጠር ከተማ ትምህርት ጀመርኩ፡፡ በቃ ምሁርነቴ አንድ ብሎ የሚጀምረው ከዚህ ነው (ድንቄም ምሁር! ማለት አይቻልም)፡፡

እኔ የምለው የትኛውስ ተመራማሪ ውጤት ላይ የሚደርሰው በሕይወቱ ከሚያጋጥመው ገጠመኝና ሁነት ተነስቶ አይደል? ስለዚህ እኔም ከሚያጋጥመኝ ነገር ተነስቼ ተመራመርኩ ማለት ነው፡፡ ልዩነቱ የእነሱን ማንም ሲቀበለው የኔን ማንም ከቁም ነገር ላይቆጥረው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የምርምሬን ውጤት እናገራለሁ (ጉረኛ የሚል ስድብ አልፈራም)፡፡ በነገራችን ላይ ጥናቱ የተሰራው ለበርካታ ዓመታት ሲሆን ምንም ዓይነት ወጭ ግን አላወጣሁበትም (ይህኔ ነው ድንቄም ተመራማሪ ማለት)፡፡ ለምን መሰላችሁ ጥናቱ በባህሪው በማስተዋል (በምልከታ) ብቻ የሚሰራ ስለሆነ ነው፡፡ የግድ መጠይቅ መበተን አለብህ ካላችሁኝ ለሚቀጥለው ጥናት እጠቀማለሁ፡፡ ሌላው ደግሞ የሚገርመው ጥናቱ የተሰራው በሁለት ቃላት ላይ ብቻ ነው፡፡ አሁን ወደ ገለፃ ልገባ ነው (መፍትሄ ግን የለውም)፡፡

«አራዳ» ማለት ምን ማለት ነው? «ፋራ» ማለትስ?

እንዳልኩት የማንንም ሀሳብ አልጠቀምም (ማጣቀሻ የሌለው የመጀመሪያው ጥናት)፡፡ በእነዚህ ቃላት ላይ ለሚደርሰው የትርጉምም ሆነ የሌላ ስህተት ሀላፊነቱን እወስዳለሁ፡፡ በቅድሚያ ግን አራዳነትም ይሁን ፋራነት የትክክለኛ ትርጉም ይህ ነው ብሎ ያስቀመጠ የለም /እኔ የመጀመሪያው ባልሆንክ አትሉም/፡፡

በተለምዶ የምንሰማቸው ግን እንጥቀስ ከተባለ ፋራ የሚባለው ከገጠር አካባቢ የመጣና ለነገሮች አዲስ የሚሆን፣ ነገሮች በቀላሉ የማይገቡት፣ ከሰው ጋር ቶሎ የማይግባባ፣ የያዘውን ነገር (ባሕል፣ አነጋገር ወዘተ) ቶሎ የማይቀይር ሲሆን አራዳ ማለት ደግሞ የነዚህ ሁሉ ተቃራኒ ማለት ነው፡፡ እንግዲህ አራዳነትንም ሆነ ፋራነት እገሌ የተባለ ምሁር እንዲህ ነው ብሎ ትርጉም ሰጥቷል የሚለኝ ካለ ከትልቅ ምስጋና ጋር ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፡፡ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ግን ሁለቱም በተለምዶ ከሚታወቁበት ትርጉማቸው ወይም ተቃራኒ የሆነ ትርጉም እሰጠዋለሁ፡፡ ይህም ከሜዳ ተነስቶ ሳይሆን አራዳ ወይም ፋራ የሚባሉ ሰዎችን ባሕሪ ካየን በኋላ ትርጉሙ ምን እንደሚሆን አብረን መወሰን እንችላለን፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ይባልልኝ፡፡ «ፋራ» የሚለው ቃል በአዕምሯችን ውስጥ መጥፎ ትርጉም ያዘለ ስለሆነ ቃሉን ሌላ ትርጉም መስጠት ሊከብድ ይችላል፡፡ ግን እስኪ ከባሕሪያቸውና ከድርጊታቸው ተነስተን ትርጉም መስጠት እንጀምር፡-

1. አራዳ ማለት አጭበርባሪ ማለት ነው

አንድ ሰው ሰዎችን የማታለል ወይም የመሸወድ ችሎታ ካለው እሱ አራዳ ነው ሲባል እንሰማለን፡፡ ለምሳሌ ረዘም ያለ ሰልፍ ካለበት መገልገያ አካባቢ የመጣ ሰው እንደምንም አጭበርብሮ ቀድሞ በመግባት ቢገለገል አራዳ ነው ይባላል፡፡ ለምን ተብሎ እንኳን ቢጠየቅ ‹እንዲህ ሆኖ ነው፣ እዚህ ቆይቼ አሁን ወጣ ብዬ ነው ወዘተ…› እያለ በማጭበርበር የፀጥታ አስከባሪዎችንም ያታልላል፡፡ ስለዚህ አራዳ ማለት አጭበርባሪ ማለት አይሆንም?

2. አራዳ ማለት ኮራጅ ማለት ነው

አራዳ የሚባሉት ሰዎች ብዙውን ጊዜ የራሳቸው የሚባል ነገር የሌላቸውና ሌላ ላይ የሚያዩትን ለማስመሰል ብቻ የሚጥሩ ናቸው፡፡ የራሳቸው ባሕል አለባበስና አነጋገር እያሳፈራቸው በሌላ የሚቀይሩ ናቸው፡፡ ከአንድ የፊልም ተዋናይ ወይም ታዋቂ ኳስ ተጫዋች አለባበስና አረማመድ ለማስመሰል የሚታገሉ ናቸው፡፡ በተውሶ ያመጧቸውን ቃላት የምን ቋንቋ እንደሆኑ ሳያውቁ በሚያገኙበት የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ አራዳ ማለት ኮራጅ ማለት አይሆንም?

3. አራዳ ማለት ግዴለሽ ማለት ነው

አንድ ሰው ለነገሮች የማይጨነቅና ሁልጊዜ ምናባቱ ምን አስጨነቀኝ የሚል ከሆነ እሱም አራዳ ነው ይባላል፡፡ በነገራችን ላይ መጨነቅ ሲባል ውጥረት ውስጥ በመግባት ራስን ማስጨነቅ አይደለም፡፡ ግን አለብኝ ብሎ የተሰጠን ነገር በጊዜ መከወን እንጂ፡፡ አራዳ የሚባሉት ግን ለትምህርት፣ ለፈተና፣ ለተሰጠ ስራ ወዘተ የማይጨነቁና ለፈተናና ለአበል ጊዜ ብቻ ብቅ የሚሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ አራዳ ማለት ግዴለሽ ማለት አይሆንም?

4. አራዳ ማለት ከዳተኛ ማለት ነው

ይህን ሐሳብ ግልፅ እንዲያደርግልኝ አንድ ምሳሌ ላንሳ፡፡ ሁለት አራዳ የሚባሉ ፍቅረኛሞች ቢኖሩ ወንዱም ካገኛት ሴት ጋር ሴቷም ካገኘችው ወንድ ጋር እንዲማግጡ የአራዳነት ሙድ የሚፈቅድ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ይህን የሚያደርግን ሰው እሱን ወይም እሷን አራዳ ነው አራዳ ነች ስለሚባል ነው፡፡ ስለዚህ አራዳ ማለት ከዳተኛ ማለት አይሆንም?

ይህን ያህል ስለአራዳነት ያልኩት እንግዲህ ከምንም አምጥቼ ሳይሆን አራዳ የሚባሉ ሰዎች ከሚያሳዩት ባሕሪና ድርጊት ብቻ ተነስቼ ነው፡፡ እኔ አልኩ ማለት ሁለንተናዊ ትርጉም አገኙ ማለት አይደለም፡፡ ይህ ትክክል አይደለም አራዳዎች እንዲህ ናቸው ለሚለኝ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፡፡ እንግዲህ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ነውና አንድ ነገር በድፍረት ልጨምር፡፡ አራዳዎች ባለጌዎች ናቸው፡፡ ሰውን ማክበር ለነሱ የበታችነት ነው፡፡ ለሰው ክብር ከመስጠት ይልቅ ሰውን መናቅና መዝለፍ ያው የዘመናዊነት መገለጫ ይመስላቸዋል፡፡

እንግዲህ ስለአራዳነት ይህን ያህል ካልኩ አሁን ደግሞ ስለፋራነት ጥቂት ልበል፡፡ እንግዲህ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት አሁንም እንደምደግመው «ፋራ» የሚባለው ቃል በስድብነቱና በመጥፎ ትርጉሙ ውስጣችን ስለተሰረፀ ትርጉሙን መቀየር ፈፅሞ የማይመስል ሊሆን ይችላል፡፡ ግን በድርጊት ስናየው ደግሞ የተሰጠውን ትርጉም የማይወክል ነው፡፡

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ቄንጠኛው (ልብወለድ) የመጨረሻ ክፍል

ከባለፈው  እትም የቀጠለ

አረጋዊ ሰለሞን AS (3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ)

Aregawisolo27@gmail.com

መድረኩ በልክ ተሰናድቷል:: የመጥሪያ ካርድ ሳይደርሳቸው በርካታ ታዳሚያን መካከል ጥቂት የማይባሉ በሰዓታቸው ተገኝተዋል:: በርካታ ተማሪዎች ወደ አዳራሹ (auditorium) ለመግባት ወረፋ ይዘዋል:: የመድረኩ ጀርባ በተንቀሳቃሽ ቁሶች ተውቧል:: ከአዳራሹ (auditorium) በር የቆሙትን ተማሪዎች በጥንቃቄ እንዲገቡ ተደረገ::

ተውኔቱ በሚቀርብበት ሰዓት ላይ ጫጫታ እንዳይኖር ሜትሮፖሎች በፀጥታው ስራ ላይ ተሰይመዋል:: ይህ የተደከመበት ዝግጅት ስኬታማ ይሆንን? እነ ቄንጠኛው ተስፋ አድርገዋል:: በተመልካች ብዛት ምክንያት አዳራሹ ጠጠር መጣያ የለውም!

ቄንጠኛው (አቤል) ሁለገብ የጥበብ ሰው ነው:: ይዘፍናል፣ ይተውናል፣ ይስላል፣ ይገጥማል:: ብዙ ጊዜ ደግሞ በተሰጥኦው ስኬታማ እንደሆነ ነው::

አያና የመተወን ተሰጥኦ ባይኖረውም የመፃፍና የማዘጋጀት ብቃት ግን ተችሮታል:: ኤርሚያስና አስመላሽ ጥሩ በሚባልበት መልኩ ይተውናሉ:: ለጥበባቸው መሰረት የሆነውን የ2ኛ ደረጃ ት/ት ቤታቸውን ያመሰግናሉ:: በሚኒ - ሚዲያና በሌሎች ክበቦች ላይ የነበራቸው ተሳትፎ ለዛሬ አብቅቷቸዋል:: ቢሆንም ግን ዩኒቨርሲው ጥበባዊ ስራዎች ላይ ትኩረት ባለመስጠቱ በእጅጉ አሳዝኗቸዋል:: ይህ ቲያትር ከመመረቃቸው እና ግቢውን ከመልቀቃቸው በፊት የሚያሳዩት የመጨረሻ ቲያትር ነው::

ቲያትሩ ከተጀመረበት ሰዓት እስካሁን ድረስ ፫(ሶስት) ትዕይንቶች ታይተዋል:: በመሆኑም ጡዘት ላይ ደርሷል:: ከተመልካቹ ገፅ ልዩ ስሜት ይነበባል:: የተዋንያኑ ብቃት አስደናቂ ሆኗል:: አያና ውስጡ ሃሴት እየተሰማው ከፊት ለፊት ወንበር ላይ ተቀምጦ ይመለከታቸዋል:: የተውኔቱ ማጀብ የሙዚቃ አመራረጥ ላይም ስኬታማ እየሆኑ ነው::…….

ቲያትሩ ከተጀመረ ከ1:30 ሰዓት በኋላ ተጠናቀቀ:: ታዳሚውም ባለማቋረጥ ሞቅ ያለ ጭብጨባ ካጨበጨበ በኋላ ትዕግስት ፈጠን ብላ ወደ መድረክ በመውጣት ሁሉንም ተዋንያን ሰላም ካለቻቸው በኋላ ቄንጠኛው ላይ ሄዳ ተጠመጠመችበት:: ታዳሚው ከተረጋጋ በኋላ ባለዕዳ የተሰኘውን ቲያትር (ተውኔት) የተጫወቱትን በሙሉ ወደ መድረክ ወጥተው ስማቸውን አስተዋወቁ:: ቄንጠኛው ማይኩን ለመጠቀም እንዲህ አለ፤

«ይህ ተውኔት እኛ መድረክ ላይ ወጥተን ተጫውትነው:: ነገር ግን እኛ ይህንን «ባለዕዳ» የተሰኘውን ተውኔት እንድንጫወት ያደረገን አንድ ትልቅ ሰው ነው:: እኛ ካላማጥንላቸው የማይወልዱ ብዙዎች ናቸው:: አይደል የሚባለው? እኛ እንወልድ ዘንድ ያማጠልን ይህ ጥበበኛ ሰው ወደ መድረክ እንዲወጣ እጋብዛለሁ::» አለና አያናን ወደ መድረክ የተሰማውንና ምኞቱን እንዲገልፅ ጋበዘው::

አጠር ደንደን ያለው ቀዩ አያና ፊቱ ላይ የደስደስ እየተነበበ "ማይኩን" ተቀብሎ ሃሳቡን መናገር ጀመረ::

«ይህን ያክል ሙገሳ እንኳን አይገባኝም ነበር፤ ቢሆንም ግን ከልብ አመሰግናለሁ:: ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ክፋትን የሚያደርግ ሰው እንዳለ ሁሉ ደግ ሰውም ብዙ አለ፤ ምንም እንኳን የደግነቱ መጠን ቢለያይም ደግ ያው ደግ ነው:: እኛ ኢትዮጵያዊያን ስንጉዳ የሚደርስልንና የምንደርስለት ሰው ቢኖርም ከጉዳት በፊት የምናደርገው ድጋፍ ግን በተለይ በአሁኑ ጊዜ በጣም አሳሳቢ እየሆነ ያለ ይመስለኛል:: ታማሚን ከሚጠይቅ ይልቅ ቀብር ላይ የሚገኘው በእጅጉ ይበዛልና:: ሌላኛው ነገር ያው የሚመለከታችሁ አካላትም ስላላችሁ ፊት ለፊት ብናወራ ስለሚሻል አንድ ነገር ብል ደስ ይለኛል:: የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተብሎ የሚመጣው አልያም የምናየው አካል ሱፍ ለብሶ ባህላችንን እንጠብቅ ይላል:: እንዴት ተብሎ ነው በወሬ ብቻ ነገሮችን የምናከናውነው:: ህንዶች ለሃገራቸውና ለባሕላቸው ያላቸውን ፍቅር ከማንም በላይ ነው:: የትም ቢሄዱ አለባበሳቸውን አይቀይሩም:: ለሃገራቸውም ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ:: እኛ ግን አገራችንን እንወዳለን እንላለን ብዙዎቻችን ግን ታሪካችንን እንኳን አናውቅም:: እንደኔ እንደኔ ስለሀገሩ ታሪክ የማያውቅ አገር የለውም ባይ ነኝ:: ለማንኛውም ወቀሳ እንዳይመስለን ጉዳዩ ስለሚያቆስለኝ ነው::

«እኛ ካላማጥንላቸው የማይወልዱ ብዙዎች ናቸው አይደል ያለው ቄንጠኛው እውነቱን ነው:: እኛን የሚጠብቁ ሰዎች ከኛ ትንሽ መንገድ ይፈልጋሉ:: መንገዱን ካገኙት በኋላ ግን ከኛ በላይ ያደርጋሉ:: እናም መንገዱን ልናሳያቸው እንጂ መንገድ ሊጠፋን አይገባም:: ስለጥንካሬን እና ስይጥንናን ለይተን እንወቅ:: አሁን የተግባር ሰዎች የምንሆንበት ጊዜ ነው ስለዚህ አገራችንን ከፍ እናድርጋት ግሩም ስራ እንስራ::

- የቋን ተማሪዎች ሺህ ፍቅር እስከ መቃብሮችን ፅፈን እናስነብብ
- የምህንድስና ተማሪዎችም ሰማይ ጠቀስ ጎጆ ቤት እንስራ:: ቻይኖች ይህን ያህል አድገው እንኳን የቤት አሰራር ስለታቸው አሁንም እንደዛ ነው::
- የቲያትር ተማሪዎችና የፊልም ጠቢባን አገር አገር የሚሸቱ ነገሮች ስሩና አሳዩን:: ጋዜጠኞችም የአገራችንን በጎ ገፅታ ለዓለም አሳዩልን:: ሁላችንም በየስራ ዘርፋችን እንጠንክር:: አመሰግናለሁ:: በመጨረሻ ግን ትልቅ ፕሮጀክት አቅደናል:: ለወገን ደራሽ ወገን ነውና ከጎናችን ሁኑልን ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው! አመሰግናለሁ::»

አያና በስሜት ይህንን ከተናገረ በኋላ ማይኩን ለቄንጠኛው (አቤል) ሰጠው:: አንድ ሙዚቃ እንዲያቀርብም እንደመለመን ብሎ ጠየቀው:: ከዚያመ ወደ ነበረበት ቦታ ተመለሰ::

ቄንጠኛውም ማይኩን ተቀብሎ«አቤል እባላለሁ:: ጓደኞቼ ቄንጠኛው ብለው ነው የሚጠሩኝ:: ለዚህ ያበቁኝን ጓደኛዬ አያናንና የስነ-ዜጋ መምህሬ መ/ር ጌትነትን እንዲሁም ሁላችሁን እያመሰገንኩኝ የመወዳት የንዋይ ደበበን ዘፈን አብረን እንዘፍናለን::» ሙዚቃው ተጀመረ……

«የክብሬ መመኪያ ደስታና ሕይወቴ

ሌላ ምን ሃብት አለኝ አገሬ ናት ሃብቴ

እሰዬ…. እሰይ እሰይ…. ዛሬም እሰዬ

ነገም እሰዬ ኢትዮጵያ እምዬ…..»

ታዳሚው በደስታ እየወጣ መጨፈር ጀመረ:: የበላይ አካላትም እነ ቄንጠኛው የሚያደርጉትን ስራ ለመደገፍ ቃል ገብተው ተሰናበቷቸው:: በርካታ ታዳሚም ከጎናቸው እንደሆኑ መሰከሩላቸው:: የነ አያና ጅማሬ በመሳካቱም ትልቅ ስራ እንደሚጠበቅባቸው በማሰብ በደስታ ተቃቀፉ::

«በሌሎቹ ካምፓሶችም አሳይተን ተቀባይነት ስናገኝ ይበለጥ ጥሩ ይሆናል አሁን የተግባር ጊዜ ነው ደስ ብሎናል እንኳን ደስ ያላችሁ::» አለ የዛሬው አቤል የቀድሞው ቄንጠኛው:: ሕይወት እንዲህ ትቀጠላለች:: እነ አያናም ሃገራቸውን ለመታደግ ቆርጠው ተነስተዋል::

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!

**ተፈፀመ::**

አረጋዊ ሰሎሞን AS

Aregawisolo27@gmail.com

ማስታወሻነቱ ለአገር ወዳድ ይሁንልኝ::

አረጋዊ ሰለሞን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ ሲሆን ይህንን ቄንጠኛው የተሰኘውን ልብወለድ በናይል ጋዜጣ ለተከታታይ 9 እትሞች አቅርቧል:: የናይል ጋዜጣ አዘጋጆች ተማሪው ላበረከተው አስተዋጽኦ በዚህ አጋጣሚ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

# ሰዎች ከተናገሩት

- የመጥፎ ድርጊት መሰረቱ ገንዘብ ማጣት ነው፡፡
  (ቬርዳንድ ሽ)

- የአለማችን ውበት ሁለት ጠርዞች አሉት፡ ፡ አንደኛው «ሳቅ» ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልብን ለሁለት የሚሰነጥቅ «ሀዘን» ነው፡፡
  (ኧሩም አቪ ዋንስ ኦውን)
- ደስተኛ ሴት እንደ ደስተኛ ሀገር ታሪክ የላትም፡፡
  (ሚልኦን)
- ሕብረተሰቡ ወንጀልን ያዘጋጃል፡፡ ወንጀለኛ ወንጀሉን ይፈፅማል፡፡

  (ቡሌክ)

- እንደገና መሞከር ውርደት አይደለም፡፡ መልካም አጋጣሚነቱ ያመዝናል፡፡

  (ማርቲን ሉተር)

ዘዋሪው ወንዳለ ፈረደ

## ለፈገግታ

ባልና ሚስት መርካቶ ሱቅ ገብተው ይጠፋፉና ባል የሚስቱን ፍለጋ ያጧጥፈዋል:: በፍለጋውም መሀል አንዲት ቆንጆዬ ልጅ ያገኝና "በናትሽ ሚስቴ ጠፋችኝ ብፈልግ ብፈልግ ላገኛት አልቻልኩም፡፡ ስለዚህ አብረሽኝ ትንሽ ቆይ ይላታል::" ይኔ ያች ልጅ ግራ ተጋብታ "ለምን" ብትለው "ከቆንጆ ወጣት ጋር ከቆምኩ በየት መጣች ሳልላት ሚስቴ ከች ትላለች" ብሏት እርፍ፡፡

ዘዋሪው ወንዳለ ፈረደ

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባብያን

የናይል የካቲት ወር እትም ላይ በፊት ገጽ ላይ በወጣው የፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት ዜና ላይ የታየው የፎቶግራፍ ጥራት ችግር በህትመት ጊዜ የተፈጠረ መሆኑን እንዲሁም የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ያማክራሉ ተብሎ የቀረበው ስህተት መሆኑን እየገለጽን ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት እና ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ከፍጥረታት ዓለም

- መሣቅ የሚችል እና ሲስቅም የሚያምርበት እንስሳ ሰው ነው፡፡
- ስቃይ ሲበዛባቸው እራሳቸውን በራሳቸው የሚገድሉ እንስሳት ሰው እና ጊንጥ ብቻ ናቸው፡፡
- በጀርባው መተኛት የሚችል ብቸኛው እንስሳ ሰው ነው፡፡
- እራሳቸውን በመስታወት አይተው መልካቸውን መለየት የሚችሉ ፍጥረታት ሰው እና ቺምፓንዚ ብቻ ነው፡፡
- አርጅታም ልጅ ከመውለድ የማትነጥፍ እንስሳ ድመት ናት፡፡
- ድመት በሕይወት ዘመንዋ 100 ግልገሎች ተወልዳለች፡፡
- በድመቶች ጆሮ ውስጥ እና ዙሪያ 64 ጡንቻዎች አሉ፡፡ ስለዚህም ጆሮዋን እንደፈለገች ማዘዝና ማጣጠፍ ትችላለች፡፡
- በከፍታ ዝላይ የሪከርድ ባለቤት የሆኑት እንስሳት ፒማ እና ሊቶፓርድ የተባሉ የድመት ዝርያዎች ሲሆኑ ከ5-6 ሜትር ከፍታ መዝለል ይችላሉ፡፡
- ግመል የሐሞት ከረጢት የላትም፡፡
- ከእንሰሳት ሁሉ እጅግ በጣም ቂመኛ የምትባለው ግመል ናት፡፡
- ግመል አንድ እንስሳ ወይም ሰው ቢተናኮላት ለሰባት ዓመት ያህል ቂም ትይዛለች፡፡ በዚህ መሐል በዳይዋን ካገኘች ከመበደል (ከመጉዳት) ወደ ኂላ አትልም፡፡
- እንደ ሰው ሕልም ከሚያዘወትር እንስሳት መሀል ፈረስ ዋነኛው ነው፡፡
- አያድርስ እንጂ የኒውክሌር ቦምብ ፍንዳታ ቢከሰት መርዙን ተቋቁሞ በአካባቢው መትረፍ የሚችል ብቸኛ ፍጡር በረሮ ነው፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ በዝግመት ለውጥ ሂደት ምንም አይነት ልዩነት የማያሳይ ፍጥረት ቢኖር በረሮ ብቻ ነው፡፡ በረሮ ከዛሬ 300,000,000 ዓመታት ጀምሮ በምድር ላይ እንደኖረ በሳይንስ የተረጋገጠ ሲሆን በእነዚህ ረጅም ዘመናት ውስጥ ምንም አይነት ለውጥ ያልታየበት ፍጥረት ነው፡፡

- ምግብ ለመዋጥ 25 ጡንቻ
- ወደፊት ለመራመድ 52 ጡንቻ
- የዓይንን ቆብ ወደላይ ለማንሳት 30 ጡንቻ
- ለመሳሳም 20 ጡንቻ
- ለመኮሳተር 43 ጡንቻ
- ለመሳቅ 17 ጡንቻዎች በእንቅስቃሴ ላይ ይውላሉ፡፡
- በመሞት ሂደት ወቅት የሰውነታችን የስሜት ሕዋሳት ስራቸውን የሚያቆሙት በሚከተለው ቅደም ተከተል ነው - ቆዳ - አይን - ጆሮ - አፍንጫ - ምላስ
- ይህን ሂደት ስናይ የዋህ መሳዩ ቆዳ መጀመሪያ ይሞታል። ምላስ ደግሞ እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ አልሞት ባይ ተጋዳይ ሆና ይዘልቃል፡፡

ምንጭ:- የእውቀት ምህዳር ዶ/ር ኬኬ

## አራዳ እና ፋራ (ወግ)...

ከገጽ 13 የዞረ

ምናልባት እንደ አራዳነት ዘርዘር ያለ ትርጉም ባልሰጠውም እኔም ከፋራዎች አንዱ ስለሆንኩ ጠቅለል ያለ መለያውን መግለፅ እችላለሁ፡፡

«ፋራ» የሚባሉት በራሳቸው ማንነት ብቻ የሚኖሩ፣ አረንጓዴ እያዩ አረንጓዴ ነጭ ሲያዩ ነጭ የማይሆኑ ወጥ ማንነት ያላቸው ናቸው፡፡ አማረም ከፋም በራሳቸው ባሕል፣ አነጋገር ብቻ የሚኖሩ ቆራጥ ውሳኔ ያላቸው ናቸው፡፡ ለሰው ክብር የሚሰጡ ለሰው የሚያዝኑና የዋህ ናቸው፡፡ በአጭር የአራዳነት ተቃራኒ ማለት ነው፡፡ እንግዲህ የጥናትና ምርምር ውጤት ይህ ነው፡፡ ለበርካታ ዓመታት ያጠናሁት ነው፡፡ ቀልድ እንዳይመስላችሁ ጥናቱን ስሰራ እንደ አራዳም ሆኘ ነበር፡፡ ግን ስለማያዋጣ ወደ ፋራነቴ ተመልሻለሁ፡፡ በመጨረሻም ጥናቱን የሰራሁት ያለምንም ማጣቀሻ መፅሀፍ ስለነበር ምንም አልጠቅስም፡፡ ይህ ሀሳብ የኔ ነበር የሚል ካለ መፅሀፉን ያሳየኝ፡፡ ሌላ ጊዜ በሌላ የጥናት ውጤት እስከምንገናኝ እዚህ ላይ አበቃለሁ፡፡ (ጥያቄ ካለ በውስጥ መስመር)፡፡

# አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር














ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ